**ምዕራፍ አንድ**

**ስለ ራሳችን**

# 1.1 *ምግባችን*

ለሰው ልጅ ለመኖር የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ነገሮች ምን ምን ናቸው;

በቤታችሁ ምን ምን እንደምትመገቡ አንድ በአንድ ለመምህራችሁ ተናገሩ። ምግብ ለምን ያስፈልጋል?

የምግብ ጥቅም


ሕይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ ለመኖር ምግብ ያስፈልጋቸዋል። ምግብ ለሰው ልጅ በሚሠጠው ጥቅም በሦስት ይከፈላል። እነርሱም፣

1. ሰውነት ገንቢ ምግቦች
2. ጉልበት እና ሙቀት ሰጪ ምግቦች
3. በሽታ ተከላካይ ምግቦች

**1.** ሰውነት ገንቢ ምግቦች

ምግብ ለእድገት እና ለሰውነት ግንባት በጣም ያስፈልጋል። ሰውነታችን እንዲያድግ እና እንዲፋፋ እንዲሁም እንዲገነባ የሚረዱ የተለያዩ የምግብ አይነቶችን ቀን በቀን ማግኘት አለበት።

የመወያያ ጥያቄዎች
ከእፅዋት የሚገኙ ለሰውነት እድገት እና ግንባታ የሚያገለግሉ የምግብ አይነቶች የትኞቹ ናቸው?





*ሥዕል 1:1* ለሰውነት እድገት እና ግንባታ የሚጠቅሙ ከእፅዋት የሚገኙ የምግብ አይነቶች


**ጥያቄ፡** ለሰውነት ግንባታ እና እድገት የሚያገለግሉ ከእንስሳት የሚገኙ የምግብ አይነቶችን ዘርዝሩ።







ወተት የበግ ሥጋ የበ_ ሥጋ







ዓሣ የዶሮ ሥጋ እንቁላል

*ሥዕል 1.2* ለሰውነት ግንባታ እና እድገት የሚያገለግሉ ከእንስሳት የሚገኙ የምግብ አይነቶች።


ለሰውነት እድገት እና ግንባታ ከሚጠቅሙ የምግብ አይነቶች ውስጥ አንዱ ወተት እና የወተት ተዋፅኦ ናቸው።


የመወያያ ጥያቄዎች

የወተት ተዋፅኦ ምን ምን ናቸው? እንዴት እንደሚዘጋጁ ወላጆቻቸሁን በመጠየቅ ለክፋላችሁ ዘገባ አቅረቡ።

የወተት ምንጭ የሆኑትን እንስሳት ሥም ዘርዝሩ።

ወተት ለሕፃናት በጣም አስፈላጊ ነው። በቂ ወተት አግኝተው ያደጉ ሕፃናት ጠንካራ ሰውነት፣ ብሩህ አዕምሮ እና በሽታን የመቋቋም ችሎታ አላቸው።






ላም ግመል

*ሥዕል 1:3* የወተት ምንጭ የሆኑ እንስሳት

## 2. ጉልበትና እና ሙቀት ሰጪ ምግቦች፣

ጉልበት ሠጪ የምግብ ዓይነቶች ምን ምን ናቸው;



Qamadii | Boqqolloo Mixaaxisa Shonkaraa

Dinnicha ድንች Cooma ጮማ Dhadhaa ቅቤ

ሥዕል 1:4 ጉልበት እና ሙቀት ሰጪ ምግቦች

ከምግብ የሚገኝ ጉልበት የሰው ልጅ የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውን ይረዳል።



Taphachuu Qotuu hojii waajjira

ስዕል 1:5

## 3. በሽታ ተከላካይ ምግቦች

ሰውነታችንን ከበሽታ የሚከላከሉ የምግብ አይነቶች እነ ማን ናቸው?



ማንጉ አናናስ አፕል

paappayaa ቲማቲም Timaatima ፓፓያ

*ሥዕል 1:6* በሽታ ተከላካይ የምግብ አይነቶች

ሰው ለመኖር ጤናማ መሆን አለበት። ጤናማ ለመሆን ደግሞ በሽታ ተከላካይ ምግቦችን መመገብ አለበት።

መልመጃ **1.1**

በሚከተለው ሠንጠርዥ ውስጥ የተዘረዘሩትን የምግብ አይነቶች ምድባቸውን

የ"(**X**)" ምልክት በማድረግ አሳዩ።

| *ተ.ቁ* | *የምግብ አይነት* | *ለሰውነት እድገትና ግንባታ* | *ጉልበትና እና ሙቀት ሰጪ* | *በሽታ ተከላካይ* |
|---|---|---|---|---|
| 1 | *ዳቦ* | | **X** | |
| 2 | *ሥጋ* | | | |
| 3 | *ዓሣ* | | | |
| 4 | *ቅቤ* | | | |
| 5 | *ድንች* | | | |
| 6 | *ጥቅል ጎመን* | | | |
| 7 | *ብርቱካን* | | | |
| 8 | *ሙዝ* | | | |
| 9 | *እንቁላል* | | | |
| 10 | *ዘይት* | | | |
| 11 | *አተር* | | | |
| 12 | *ባቄላ* | | | |
| 13 | *ቆሎ* | | | |
| 14 | *ወተት* | | | |
| 15 | *ጎመን* | | | |
| 16 | *ቀሪያ* | | | |

የሚዘወተሩ ምግቦች


የውይይት ጥያቄዎች **:**

በአካባቢያችሁ የሚዘወተሩ የምግብ አይነቶችን በመዘርዘር ክፍል ውስጥ ተወያዩ። ከምን እንደሚዘጋጁም ቤተሠቦቻችሁን በመጠየቅ ጽፋችሁ ለክፍል ተማሪዎች አንብቡላቸው።

## የምግብ ምንጮች

### ሀ. ሰብሎች


በአካባቢያችሁ ለምግብ ምንጪነት የሚያገለግሉ የእህል አይነቶችን ዘርዝሩ፡-



ስንዴ
Qamadii



አጃ



ቦሎቄ



በቆሎ




ጤፍ



ገብስ






እንሰት                                  አተር


ሥዕል 1:7  የምግብ ምንጭ የሆኑ የእህል አይነቶች

## ለ. እንስሳት


በአካባቢያችሁ ለምግብነት የሚያገለግሉ እንስሳትን ዘርዝሩ




ዶሮ



ላም



ሰንጋ



በግ





ግመል                                   ፍየል

ሥዕል 1:8 የምግብ ምንጭ የሆኑ እንስሳት

ሥጋ፣ እንቁላልና ወተት ከእንስሳት የሚገኙ የምግብ አይነቶች ናቸው።

## የአመጋገብ ሥነ ሥርዓት

### የውይይት ጥያቄዎች

### የአመጋገብ ሥነ-ሥርዓት ምንድነው? የአመጋገብ ሥርዓት እንዴት ይጠበቃል?

ከምግብ በፊት፣ በምግብ ጊዜ እና ከምግብ በኋላ ሊጠበቁ በሚገቡ የአመጋገብ ሥርዓቶች ላይ በቡድን ተወያዩ።

### ከምግብ በፊት ያለው ሥርዓት፡-

- እጃችንን በሣሙና መታጠብ
- ንጹህ የመጠጥ ውሃ ማዘጋጀት
- ምግብ  ተንጠባጥቦ ልብሳችንን እንዳያበለሽ አስቀድሞ መጠንቀቅ

የምግብ ጊዜ ሥርዓት፡-

- ማላመጥ የምንችለውን ያህል መጉረስ
- አብረውን ከሚመገቡ ሰዎች ጋር በሥርዓት መመገብ
- ቀስ ብሎ መመገብ
- እየተመገቡ ወይም ምግብ እያለመጡ አለመሳቅና
- የሚበቃንን ያህል ብቻ መመገብ

ከምግብ በኋላ ያለው ሥርዓት፡-

- እጆቻችንን በሣሙና መታጠብ
- አፋችንን መጉመጥመጥ
- የተመገብንባቸውን እቃዎች አጥበን በሥርዓቱ ማስቀመጥ
- የተመገብንበትን ቦታ ማጽዳት



*ሥዕል 1: 9 የአመጋገብ ሥነ-ሥርዓት*

**መልመጃ 1.2**

ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ/ሺ።

1. የምግብ ጥቅም የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ጉልበት እና ሙቀት መስጠት. ለ. ለእድገትና ለሰውነት ግንባታ

ሐ. በሽታ ለመከላከል መ. ሁሉም መልስ ነው

2. በሽታ ተከላካይ ያልሆነ የምግብ አይነት የቱ ነው?

ሀ. ፓፓያ ለ. ቲማትም ሐ. ሙዝ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

3. ጉልበት እና ሙቀት ሰጪ የሆነው የምግብ አይነት የቱ ነው?

ሀ. ድንች ለ. ቲማትም ሐ.ማንጎ መ. ጐመን

4. ከእፅዋት የሚገኘው የምግብ አይነት የቱ ነው?

ሀ. ጮማ ሐ. አተር

ለ. ቅቤ　　　　　　　　　　መ. ወተት

5. ጥሩ የአመጋገብ ስርዓት ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. በችኮላ መመገብ　　　　　　　　ሐ. ቀስ ብሎ መመገብ

ለ. እጅ ሣይታጠቡ መመገብ　　　　መ. ሀ ና ለ ትክክል ናቸው

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጥ/ጪ።

1. ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት የምግብ አይነቶች ውስጥ ከእፅዋትና ከእንስሳት የሚገኙ ብለህ/ሽ መድብ/መድቢ። መኮሮኒ፣ ቅቤ፣ ዳቦ፣ እንቁላል፣ እንጀራ፣ ጨማ

2. ከዚህ በታች የሚገኙትን የአትክልት፣ የፍራፍሬና የእህል አይነቶችን ስዕል በማንሳት መግለፅ የሚችሉ ቀለማትን በመቀባት ክፍላችሁ ውስጥ ለጥፍ/ፊ. ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ጐመን፣ ቲማቲም፣ ስንዴ፣ ማንጐ

# 1.2 ጤናችን

የወይይት ጥያቄዎች

ጤንነት ማለት ምን ማለት ነው;

በአካባቢያችሁ የታመመ ሰው አይታችሁ ታወቃላችሁ?

በኑሮ ውስጥ ሰውን የሚያስደስተው ምንድነው? ምንስ ያስከፋዋል? በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ሰዎች ለርስ በርሳቸው የሚመኙትና የሚጠያየቁት ምንድነው? ሳይገናኙ ለብዙ ጊዜ የቆዩ ሰዎች ሲገናኙ ምን ይጠያየቃሉ? በቡድን ተወያዩ።

የፕሮጀክት ሥራ: **1.1**

በቀበሌያችሁ ውስጥ ወደሚገኘው የጤና ጣቢያ ወይም ኬላ በመሄድ የጤና ባለሙያ በማነጋገር የጤና ምንነት፣ በሽታ መከላከል፣ የበሽታ  በቤተሰብ ላይ የሚያመጣውን ጉዳት ምን እንደሆነ በመጠየቅ ለክፍል ዘገባ በማቅረብ ተወያዩበት።

ጤንነት ማለት ውስጣዊ፤ ውጫዊና ማህበራዊ ደህንነት ማለት ነው። በሕብረተሰብ ኑሮ ውስጥ ጤና ወሳኝ ነገር ነው። ጤንነቱ የተጠበቀ ሰው፡-

- አካላዊ ጤንነቱ የተጠበቀ ነው
- ጥሩ ማህበራዊ ግንኙነት አለው።
- ጠንካራ ነው
- በኑሮው ደስተኛ ነው።

ሙሉ ጤንነት እንድኖረን ከሚያስፈልጉን ነገሮች የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል።

- የግል ንጽህናን መጠበቅ
- በሰው ጤንነት ላይ ጉዳት ከሚያደርሱ ነገሮች እራስን መጠበቅ

- የመኖሪያ አካባቢያችንን ንጽህና መጠበቅ
- ተመጣጣኝ ምግብን መመገብና የመሳሰሉት ናቸው።

አንድ ጤናማ ሰው የሚያሳየውን ምልክት ሕፃናትን እንደ ምሳሌ ወስደን እንደሚከተለው ማየት እንችላለን።

- ሙሉ ጤናማ የሆኑ ሕፃናት ንቁና ጠንካራ ናቸው።

እነዚህ ሕፃናት ደስተኞች፣ የሚጫወቱ፣ ትምህርታቸውን በንቃት የሚከታተሉና ወዘተ ናቸው።




*ሥዕል 1.10* የጤና ጥቅም

## የውይይት ጥያቄዎች

በቤተሰባችሁ ውስጥ የታመመ ሰው አይታችሁ ታውቃላችሁ? በታመመ ሰው ላይ የሚታዩ ምልክቶች ምን ምን ናቸው? ተወያዩበት።

## ሕመም /በሽታ/

ጤንነቱ የታወከ ሰው ታማሚ ወይም በሽተኛ ይባላል። ታማሚ ሰው ሥራውን በሥርዓቱ ማከናወንና ሌላ ሰውን መርዳት አይችልም።



*ሥዕል 1.11* *ታማሚ /በሽተኛ/ ሕፃን*

በታመመ ሰው ላይ የሚታዩ ምልክቶች፡- ትኩሳት፣ ራስ ምታት፣ የምግብ ፍላጐት ማጣት፣ ድካም፣ ተቅማጥ፣ ትውከት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

እንዲህ አይነት ስሜት ስሰማችሁ ለጓደኞቻችሁ፣ ለመምህራችሁ ወይም ለወላጆቻችሁ በመንገር መታከም አለባችሁ፡፡

## *መልመጃ* 1.3

1. ጤንነት ማለት ምን ማለት ነው?
2. በታማሚ ሰው ላይ ከሚታዩ ምልክቶች ውስጥ ሦስቱን ጥቀስ/ሺ፡፡
3. በጤናማ ሰው ላይ ከሚታዩ ምልክቶች ውስጥ ሦስቱን ጥቀስ/ሺ፡፡
4. የሕመም ስሜት ሲሰማህ/ሽ ምን ማድረግ እንዲለብህ/ሽ ጻፍ/ፊ፡፡
5. ጤንነቱ የታወከ ሰው ምን ይባላል?

# 1.3 የግል ንጽህናችንን መጠበቅ

ጥያቄዎች፡-

የግል ንጽህናን አስመልክቶ በአንደኛ ክፍል የተማርከውን/ሽውን ታስታውሳለህ/ሽ; የግል ንጽህና ማለት ምን ማለት ነው? የግል ንጽህናን መጠበቅ ምን ጥቅም አለው?

የግል ንጽህናህን/ሽን ለመጠበቅ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩ ነጥቦች

መተግበር አለብህ/ሽ፡፡

1) ጧት ቁርስ ከመብላት በፊት እጃችንና ፊታችንን መታጠብ

2) ሁልጊዜ ከምግብ በፊትና በኋላ እጅ መታጠብና አፍን መጉመጥመጥ

3) ከሽንት ቤት መልስ እጅን በሣሙና መታጠብ

4) ማታ ማታ እግርን መታጠብ

5) በሳምንት አንድ (ሁለት) ጊዜ ገላን መታጠብ

6) የሌሊትና የቀን ልብሶችን ንጽህናቸውን መጠበቅ

7) ጥፍርን መቁረጥና የመሳሰሉት

ጤንነታችንን ለመጠበቅ የግልና የአካባቢያችን ንጽህና መጠበቅ አስፈላጊ ነው።

የውይይት ጥያቄ፡

በግል የምትጠቀሙባቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ተወያዩባቸው።

ሰውነታችንና በግል የሚንጠቀምባቸውን ነገሮች በንጽህና መጠበቅ የግል ንጽህና መጠበቅ ይባላል።

## የእጆቻችንን ንጽህና መጠበቅ

በእጆቻችን ምን ምን ነገሮችን እንይዛለን? በእጆቻችን የምንይዛቸው ነገሮች ሁሉ ንጹህ ናቸው?

በሽታን ሊያሲዙን የሚችሉ በዓይን የማይታዩ ተዋሲያን /ጀርሞች/ በእጆቻችን ላይና በጥፍሮቻችን ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ። ስለዚህ እጆቻችንን በሣሙና መታጠብና ጥፍሮቻችንን በመቁረጥ ንጽህናችንን መጠበቅ አስፈላጊ ነው።

በንጽህና ጉድለት ሊመጡ የሚችሉ በሽተዎች ምን ምን ናቸው?

እከክ፣ ወስፋት፣ ትራኮማና የመሳሰሉት በግል ንጽህና ጉድለት ሊመጡ የሚችሉ በሽተዎች ናቸው።

የፊት ንጽህና መጠበቅ

ንጽህናው ያልተጠበቀ ፊት ለበሽታ የተጋለጠ ነው። ስለዚህ የፊታችን ንጽህና ሁልጊዜ መጠበቅ አስፈላጊ ነው።



ሥዕል 1.13 ፊትን መታጠብ

## የአፋችንና የጥርሳችንን ንጽህና መጠበቅ

ከመመገባችሁ በፊትና በኋላ አፋችሁን ትጉመጠመጣላችሁ?

የጥርሳችሁን ንጽህና ለመጠበቅ ምን ታደርጋላችሁ?



ሥዕል **1.14** ጥርስ መፋቅ /መቦረሽ/

## የእግር ንጽህናን መጠበቅ

ማታ ማታ ሁልጊዜ እግራችሁን ትታጠባላችሁ?

ካልሲያችሁንስ ታጥባላችሁ?



ሥዕል 1.15 እግር መታጠብ

## የገላችንን ንጽህና መጠበቅ

በሙቀት ጊዜ፣ በሥራና በጫወታ ጊዜ ሰውነታችንን ያልበናል። በዚህ ጊዜ በቆዳችን ላይ ባሉት ቀዳዳዎች አማካኝነት ቆሻሻ ከሰውነታችን ውስጥ በላብ ይወጣል። ላብና ቆሻሻ በሰውነታችን ላይ ሲጠራቀም ተዋሲያን/ጀርሞች/ በሰውነታችን ላይ እንዲራቡ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር በሰውነታችን ላይ ጉዳት ያስከትላሉ። ስለዚህ ገላችንን በየጊዜው መታጠብ አስፈላጊ ነው።



ሥዕል 1.16 ገላችንን መታጠብ

## የፀጉር ንጽህና መጠበቅ

የፀጉራችን ንጽህና ካልተጠበቀ እንደ ቅማልና ቅጫም የመሳሰሉት ተባዮች በፀጉራችን ውስጥ ይራባሉ። እነኚህ ተባዮች ደግሞ ለተለያዩ በሽታዎች ያጋልጡናል። ስለዚህ ቢያንስ በሳምንት ሁለት ጊዜ ፀጉራችንን መታጠብ አለብን። በየቀኑ ደግሞ ፀጉራችንን በማበጠር በቂ አየር እንዲያገኝ ማድረግ አስፈላጊ ነው። እንዲሁም ፀጉራችንን በየጊዜው ማስተካከል አስፈላጊ ነው።



ሥዕል 1.17 ፀጉር መታጠብና ማበጠር

## የልብስ ንጽህና መጠበቅ

ልብሳችሁን ምን ያቆሽሸዋል? ልብሳችሁ ቢቆሽሽ ምን ታደርጋላችሁ?



*ሥዕል **1:18*** ልብስ ማጠብ

ልብሶቻችን በላብ፣ በአቧራ፣ በጭቃና በተለያዩ ነገሮች ሊቆሽሹ ይችላሉ። በቆሸሻ ልብስ ላይ እንደ ቅማል፣ ቅጫምና ቁንጫ የመሳሰሉት ተባዮች ይራባሉ።

ቁንጫና ቅማል በሽታን ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው በማስተላለፍ ጉዳት ያስከትላሉ።


ልብሶቻችንን አጥበን በፀሐይ ብርሃን እንዲደርቅ ማድረግ ይኖርብናል። ከዚያም በኋላ በካውያ በመተኮስ አስተካክለን መልበስ አስፈላጊ ነው። ልብሶቻችንን ንጽህናው በተጠበቀ ቦታ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የልብስ ንፅህና ለመጠበቅ የሚከተሉትን ማድረግ ይኖርብናል።

- የመኖሪያ አካባቢያችንን ማጽዳት
- የመማሪያ ክፍላችንንና የትምህርት ቤት ግቢያችንን ንጽህና መጠበቅ
- መጸዳጃ ቤትን በንጽህና መጠቀም
- የሰውንና የእንስሳትን መኖሪያ መለየት
- ቆሻሻ/ጥራጊ/ በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት ውስጥ መጣል።

## በንጽህና ጉድለት ሊመጡ የሚችሉ በሽታዎች

በንጽህና ጉድለት ሊመጡ የሚችሉ በሽታዎችን ዘርዝሩ።

በንጽህና ጉድለት ሊመጡ የሚችሉ በሽታዎች ብዙ ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ እከክ፣ የወስፋት ትል፣ ትራኮማና ተቅማጥ በብዛት የሚታወቁ ናቸው።



ሥዕል 1.19 በንጽህና ጉድለት ለእከክ የተጋለጠ ህፃን

ኤች አይ ቪ /ኤድስ/

ስለ ኤች አይቪ /ኤድስ በሽታ ምን ታውቃላችሁ?

ኤች አይ ቪ /ኤድስ ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፍ በሽታ ነው። የመተላለፊያ መንገዶቹም የሚከተሉት ናቸው።

1. በደም ንክኪ.

2. ስለታማ መሣሪያዎችን በጋራ በመጠቀም ለምሳሌ መርፌ፣ ምላጭ፣ ወስፌና የመሳሰሉት ናቸው።.

የኤች አይ ቪ /ኤድስ/ መከላከያ ዘዴዎች፡-

- ከደም ንክኪ መጠንቀቅ
- ስለታማ መሣሪያዎችን በጋራ አለመጠቀም

### መልመጃ **1. 4**

ሀ**.** ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ/ሺ።

1. ሙሉ ጤናማ ለመሆን የሚጠቅመው የቱ ነው?

ሀ. የግል ንጽህና መጠበቅ

ለ. ተመጣጣኝ ምግብ መመገብ

ሐ. አካባቢያችንን በንጽህና መጠበቅ

መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

2. ጤናማ ያልሆነ ሰው የሚያሳየው ምልክት ምንድነው;

ሀ. በትጋት መማር

ለ. የምግብ ፍላጐት ማጣት

ሐ. ደስተኛ መሆን

መ. ጠንክሮ መሥራት

3. የሕመም /በሽታ/ ምልክት የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ማስታወክ　　ሐ. የምግብ ፍላጐት ማጣት

ለ. ራስ ምታት　　መ. ሁሉም መልስ ናቸው

4. የግል ንጽህናን መጠበቅ የሚያመለክተው የቱ ነው?

ሀ. እግርን መታጠብ　　ሐ. ገላን መታጠብ

ለ. እጅን መታጠብ　　መ. ሁሉም መልስ ናቸው

5. በቆሸሸ ልብስ ውስጥ የሚራቡ ተባዮች

ሀ. ቅጫም　　ሐ. ቁንጫ

ለ. ቅማል　　መ. ሁሉም

6. የኤች አይ ቪ /ኤድስ/ በሽታ መከላከያ ዘዴ የቱ ነው?

ሀ. ከደም ንክኪ መጠበቅ

ለ. ስለታማ መሣሪያዎችን በጋራ መጠቀም

ሐ. ስለታማ መሣሪያዎችን በጋራ አለመጠቀም

መ. ሀ ና ሐ መልስ ናቸው።

ለ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት መልስ/ሺ።

1. የግል ንጽህናን መጠበቅ ለጤንነት አይጠቅምም።
2. ከተጸዳዳን በኋላ እጃችንን በሣሙና መታጠብ አያስፈልግም።
3. ሰውነታችንን ባንታጠብ ምንም ችግር አያስከትልም።
4. ጥፍሮቻችንን በየጊዜው መቁረጥ አስፈላጊ ነው።
5. የምግብ ፍላጐት ማጣት ከበሽታ ምልክቶች ውስጥ አንዱ ነው።
6. የልብሳችንን ንጽህና መጠበቅ ለውበት ብቻ ይጠቅማል።

ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልስ ስጥ/ጪ።

1. ከምግበ በፊት ካሉት የአመጋገብ ሥርዓት ውስጥ ሁለቱን ዘርዝሩ።
2. ስንመገብ መጠበቅ ካለባቸው የአመጋገብ ሥርዓት ውስጥ ሁለቱን ጻፍ/ፊ።
3. ከተመገብን በኋላ ካሉት የአመጋገብ ሥርዓት ውስጥ ሦስቱን ዘርዝሩ።

መ. ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ተግባራትን በቅደም ተከተል አስተካክለህ/ሽ ጻፍ/ፊ።

1. መጸዳጃ ቤት መሄድ
2. እጅና ፊትን መታጠብ
3. ጥርስ መፋቅ /መቦረሽ/
4. ጧት ከእንቅልፍ መነሳት
5. ቁርስ መብላት

# ምዕራፍ ሁለት
# የአካባቢያችን ኅብረተሰብ

## 2.1 *የአካባቢያችን ኅብረተሰብ አባላት*



*ሥዕል 2:1* በተለያዩ ደረጃና እድሜ ላይ የሚገኙ የኅብረተሰብ አባላት

የውይይት ጥያቄ

የአካባቢያችሁን ኅብረተሰብ አባላት፣ ሕፃናት፣ ወጣቶች፣ ልጃገረዶች፣ ጎልማሶችና አዛውንቶች በማለት በተለያዩ ምድቦች በመከፋፈል ተወያዩበት።


ኅብረተሰብ ማለት በተወሰነ ቦታ ወይም አካባቢ በህብረት የሚኖሩ ሰዎች ማለት ነው።

የአካባቢያችን ኅብረተሰብ አባላት በአራት የዕድሜ ክልል ይመደባሉ። እነርሱም ሕፃናት፣ ወጣቶች ጎልማሶችና አዛውንቶች ይባላሉ።


*ሠንጠረዥ 2.1* የአካባቢያችን ኅብረተሰብ በእድሜ ሲከፋፈሉ

| የእድሜ ክልል | የኅብረተሰብ አባላት አይነት |
|---|---|
| ከ 0- 14 ዓመት | ሕፃናት |
| ከ 15 - 30 ዓመት | ወጣቶች |
| ከ 31 - 64 ዓመት | ጎልማሶች |
| 65 እና ከዚያ በላይ | አዛውንቶች |

እናንተስ በየትኛው የእድሜ ክልል ውስጥ ትገኛላችሁ?



ሕፃን ወጣት ጎልማሳ አዛውንት



ሕፃን                ልጃገረድ              ጎልማሳ     አዛውንት

*ሥዕል 2.2 የኅብረተሰብ አባላት በእድሜ*

ከ0-14 ዓመት ያሉት የኅብረተሰብ አባላት ሕፃናት ይባላሉ። በሕፃናት እድሜ ክልል ያሉ ሁሉ በአካል ስላልጠንከሩና በአዕምሮም ስላልበሰሉ በተለያዩ ሥራ ላይ አይሠማሩም። ስለዚህ በቤተሰብ ድጋፍና እንክብካቤ ይኖራሉ።

በወጣትነትና በጎልማሳነት የእድሜ ክልል ያሉ የኅብረተሰብ አባላት በአካል ጥንካሬ፣ በአእምሮም ብሰለት አላቸው። እነኚህ አባላት በተለያዩ ሥራ ላይ በመሠማራት ገቢ ሊያስገኙ ይችላሉ። ስለዚህ እነዚህ የኅብረተሰብ አባላት ራሳቸውንና ሌሎችንም ሊያስተዳድሩ የሚችሉ ናቸው።

እድሜያቸው ከ 65 ዓመት በላይ የሆኑ የኅብረተሰብ አባላት አዛውንት ይባላሉ። እነዚህ የኅብረተሰብ አባላት በአካልና በአዕምሮ እየደከሙ ስለሚሄዱ የሌላ ህብረተሰብ አካል ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል።

ተግባር **2.1**

1. የቤተሰብህን/ሽን አባላት ከላይ በተጠቀሰው መሠረት መድባቸው /ቢያቸው።
2. በቤተሰብህ/ሽ አባላት ውስጥ በእያንዳንዱ የእድሜ ክልል ውስጥ ስንት ሰው እንዳለ ለጓደኞችህ/ሽ ተናገር/ሪ።
3. የእያንዳንዳችሁን የቤተሰብ አባላት የእድሜ ክልል መረጃ አንድ ላይ በማድረግ የቤተሰቦቻችሁን የእድሜ መረጃ/ኘሮፋይል/ አዘጋጅ/ጂ።
4. እንደ አካባቢያችሁ የኅብረተሰብ አባላት የእድሜ ክልል ምደባ የክፍላችሁ ተማሪዎች በሕፃናት የእድሜ ክልል ውስጥ ይመደባሉ? ለመምህራችሁ ንገሩ።

*መልመጃ* **2.1**

ሀ. ከዚህ በታች ያሉት ዐረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆኑ ደግሞ ሀሰት በማለት መልስ/ሺ።

1. ሕፃናት በአካባቢ ኅብረተሰብ ውስጥ ድርሻ አላቸው።
2. በመቶ አመቱ የሞተ ሰው በሁሉም የእድሜ ክልል ውስጥ አልፏል።
3. ጎልማሳ  ሕፃን  አዛውንት ቢባል ይህ ቅደም ተከተል ትክክለኛ የእድገት ሂደትን ያሳያል።

ለ. በ"ለ" ሥር ያሉትን በ"ሀ" ሥር ካሉት ጋር አዛምድ/ጂ።

| "ሀ" | "ለ" |
| --- | --- |
| 1. ከ 31- 64 ዓመት | ሀ. አዛውንት |
| 2. የ 8 ዓመት ተማሪ | ለ. ሕፃን |
| 3. ከ 65 ዓመት በላይ | ሐ. ጎልማሳ |
| 4. የ 35 ዓመት እናት | መ. ወጣት |
| 5. ከ 0 - 14 ዓመት | |
| 6. ከ 15 - 30 ዓመት | |

## የሕፃናት መብቶች

ተግባር: **2.2** መከበር ያለባቸውን የሕፃናት መብቶች ወላጆቻችሁን በመጠየቅ በክፍላችሁ ውስጥ ተወያዩበት።

የቡድን መወያያ ጥያቄዎች

የሕፃናት መብትን በተመለከተ የሚከተሉትን ርዕሰ ጉደዮች ትኩረት ሰጥታችሁ በቡድን ተወያዩበት።

- ለመኖር አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን የማግኘት መብት አላቸው፣
- ጉዳት ሊያስከትሉ ከሚችሉ ነገሮች መጠበቅ፣
- አዕምሮን ከሚያውኩና አካልን ሊጐዱ ከሚችሉ ነገሮች መጠበቅ

ከሕፃናት መብቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

እነርሱም፡

- ምግብ፣ ልብስና የመኖሪያ ቦታ የማግኘት መብት
- የመማር መብት
- በአካል ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ ከሚችሉ ሥራዎች መጠበቅ
- የመታከም መብት
- የመፈቀር /መወደድ/ መብት

- እንክብካቤ የማግኘት መብት ናቸው
- ሕፃናት በጥሩ ሁኔታ ለማደግ በቂ ምግብ፣ ልብስና ምቹ የመኖሪያ ቦታ ማግኘት አለባቸው።

- ሕፃናት ትምህርት ቤት ገብተው የመማር መብት አላቸው። ስለዚህ ወላጆች እና መንግስት ሕፃናትን የማስተማር ሃላፊነትና ግዴታ አለባቸው።



ሥዕል 2.3 ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱ ሕፃናት

በሕፃናት ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ አደጋዎችንና ሥራዎችን ታውቃላችሁ? እነኚህ አደጋዎች ምን ምን እንደሆኑ በመወያየት ለመምህራችሁ ንገሩ።

በመኖሪያ ቤት ውስጥ በሕፃናት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎች ምን ምን ናቸው?

ከሚከተሉት ነጥቦች ጋር በማነፃፀር ተወያዩባቸው።

- በእሳት መቃጣል፣
- በፈላ ውሃ ተቃጥለው መጐዳት፣
- የተላጠ የኤሌክትሪክ ሽቦ በእጅ መያዝ፣
- ንጽህናው ያልተጠበቀ ውሃ መጠጣት፣
- ተዘጋጅቶ የቆየ ምግብ መመገብ፣
- እቤት ውስጥ የተረሳ የእንስሳትና የአዋቂ ሰዎች መድኃኒት መነካካትና መጠቀም፣
- ስለታማ የሆኑ እንደ ቢላዋ፣ መጥረቢያ፣ ምላጭ፣ መርፌና የመሳሰሉትን መነካካትና መጠቀም፣
- አልኮል (የሚያሰክሩ ነገሮችን) መጣጣት፣
- በተለያዩ እንስሳት መረገጥ፣ መወጋት፣ መነከስና የመሳሰሉት በመኖሪያ ቤት አካባቢ በሕፃናት ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ጉዳቶች ናቸው።



*ሥዕል 2.4* በውሻ የመነከስ አደጋ

በሕፃናት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ሌሎች አደጋዎች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር በክፍል ውስጥ ተወያዩበት። ከሚከተሉት ውስጥ በአካባቢያችሁ የተከሰተ ችግር አለ; ተነጋገሩ። ለምሳሌ


- በመኪና መንገድ ላይ በመውጣት በመኪና መገጨት
- በወንዝና በሃይቅ መወሰድና ጉድጓድ ውስጥ መውደቅ
- ወንዝ ለመሻገር በመዝለል ወድቆ መጎዳትና መሞት
- ዛፍ ላይ ለመውጣት መሞከርና ወድቆ መጎዳት
- በሜዳ ላይ በእግር ወለሞታ መውደቅና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ።

## በትምህርት ቤት ግቢና አካባቢ በሕፃናት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎች

በትምህርት ቤት ግቢና አካባቢ በሕፃናት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎች የሚከተሉት ናቸው።

- በጨዋታ ጊዜ መውደቅና መጋጨት
- ከጓደኞች ጋር መጣላትና መጎዳት
- ለመግባትና ለመውጣት ሲባል የትምህርት ቤት አጥር በመሹለክ በሽቦ መያዝና በመጫጫር መጎዳትና የመሳሰሉ ናቸው።

ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ በትምህርት ቤትህ/ሽ የደረሰብህ/ሽ ጉዳት አለ?



*ሥዕል 2.5* በትምህርት ቤትና አካባቢ በሕፃናት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶች

መልመጃ **2.2**

ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ "ሐሰት " ብለህ/ሽ መልስ/ሽ።

1. መብት ማለት ሁሉን ነገር አስቀድሞ ለራስ መውሰድ ማለት ነው።
2. ሕፃናት መብት እንዳላቸው ሁሉ ግዴታም አለባቸው።
3. ሕፃናት የመታከም መብት አላቸው።
4. በሕፃናት ላይ ጉዳት የሚደርሰው በመኖሪያ ቤት አካባቢ ብቻ ነው።
5. ጓደኞችን እና ታላላቆችን ማክበር ጥሩ ነው።

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጥ/ጪ።

1. ሕፃናት ሊኖራቸው ከሚችሉ መብቶች ውስጥ አራቱን ጥቀስ/ሽ።
2. በሕፃናት ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ ከሚችሉ ነገሮች ሦስቱን ጥቀስ/ሽ።
3. በመኖሪያ ቤት አካባቢ በሕፃናት ላይ ሊደርሱ ከሚችሉ አደጋዎች ውስጥ ሦስቱን ጥቀስ/ሽ።

## የሕፃናት መብት ጥሰትና መብቶቹ የሚከበሩበት መንገዶች

የቡድን ውይይት ጥያቄ

በእናንተ አካባቢ የሕፃናት መብት የሚጥሱ ተግባራት ምን ምን ናቸው? ተወያዩበት

ብዙ የሕፃናት መብት ጥሰቶች አሉ። እነርሱም፡

- ትኩረት ማጣት
- በአካል ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ቅጣቶች
- አዕምሮን የሚጐዳ ስድብ እና ውግዘት
- በሕመም ጊዜ ሕክምና ማጣት
- መደፈር
- ያለ እድሜ ጋብቻ
- የሴት ልጆች ግርዛት
- የትምህርት ዕድል ማጣት
- ከአቅም በላይ የሆኑ ሥራዎችን ማሠራትና የመሳሰሉት ናቸው።





ሥዕል 2.8 የሕፃናት አካላዊ ቅጣት

መልመጃ **2.3**

1. ሕፃናት በቤተሠብ እና በሕብረተሰቡ ውስጥ እንዴት እንደሚጨቆኑ በክፍል ውስጥ በጭውውት አሣዩ።
2. የመብት ጥሰት የደረሠባቸው ሕፃናት ለማን ማመልከት አለባቸው?
3. የህፃናት መብቶች በምን ሁኔታ ሊከበሩ ይችላሉ?

የህፃናት መብት ጥሰትን መከላከል

የሕፃናት መብቶችን ለመጠበቅ መፈፀም የሚገባቸው ተግባራት የሚከተሉት ናቸው። እነሱም፡-

- ስለ ሕፃናት መብት አካባበር ለቤተሠብ በቂ ግንዛቤ ማስጨበጥ
- ስለ ሕፃናት መብት አስመልክቶ ለተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በቂ ግንዛቤ መስጠት
- የሕፃናት መብቶች ጥሰት ሲፈፀሙ ለሕግ አስፈፃሚዎች ጥቆማ ማድረግና የመሳሰሉት ናቸው።

በአካባቢያችን ተጨባጭ ሁኔታ የሕፃናት መብት ጥሰት ጥቆማ የሚቀርብባቸው አካላት አሉ። እነርሱም፡-

- የቀበሌ መስተዳደር
- የትምህርት ቤት አስተዳደር
- ፖሊስ ጣቢያ
- የሕፃናት እና ሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት
- የወረዳ/ የከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት




*ሥዕል 2.9 ሕፃናትን ከአቅም በላይ ማሠራት*

*መልመጃ* **2.4**

ሀ**.** የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ።

1. ሕፃናት የመማር መብት አላቸው።
2. የሕፃናት መብት የሚጣሰው በጉልበት ብዝበዛ ብቻ ነው።
3. ሕፃናት ለጠየቁት ጥያቄ መልስ የማግኘት መብት አላቸው።
4. ሕፃናት ቤተሰቦቻቸውንና ሌሎች ሰዎችን ማክበር አለባቸው።

ለ**.** ለሚከተሉት ጥየቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጥ/ጪ።

1. ከዚህ በታች ካሉት ውስጥ የሕፃናት መብት ጥሰት የሆነው የቱ ነው?

ሀ. በቂ ልብስ ማጣት
ሐ. በቂ ምግብ ማጣት
ለ. የትምህርት ዕድል ማጣት
መ. ሁሉም መልስ ናቸው

2. የሕፃናትን የመማር መብት የሚጥስ ተግባር የቱ ነው?

ሀ. ሕፃናትን ከትምህርት ቤት ማስቀረት

ለ. ከእኩዮቻቸው ጋር እንዳይጫወቱ መከልከል

ሐ. ሕፃናትን መቅጣት

መ. ሕፃናትን አለማዳመጥ

3. የሕፃናት መብት በማን ሊጣስ ይችላል?

ሀ. በሚያሳድጓቸው የቅርብ ዘመድ

ለ. በቤተሰብ

ሐ. ለማሳደግ ኃላፊነት በወሰደ ሰው

መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

4. የሕፃናት መብት ጥሰት ድርጊትን ለማን ማመለከት ይኖርብናል?

ሀ. ለአስተዳደር ጽህፈት ቤት

ሐ. ለፖሊስ ጣቢያ

ለ. ለትምህርት ቤቶች አስተዳደር

መ. ሁሉም መልስ ናቸው.

ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጥ/ጪ።

1. ከሕፃናት መብት ጥሰት ውስጥ ሦስቱን ጥቀስ/ሺ።
2. የሕፃናትን መብት ለማስከበር ከሚንጠቀምባቸው ዘዴዎች ውስጥ ሁለቱን ጥቀስ/ሺ።

## 2.2 በህብረተሰብ ውስጥ መኖር

ሕፃናት የህብረተሰቡ አባል በመሆን ከህብረተሰቡ ጋር ይኖራሉ። በዕለት ተዕለት ኑሮአችን ውስጥ ማከናወን ያለብንን ሥራ ከጊዜ ጋር አጣጥመን ማቀድ ይኖርብናል።

የውይይት ጥያቄዎች

እቅድ ምንድነው; በእቅድ ውስጥ መካተት ያለባቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው? ተወያዩበት።

እቅድ ወደ ፊት የሚናከናውነውን ነገር የሚናዘጋጅበት ዘዴ ነው።

### የዕለት ተግባራትን ማቀድ

የውይይት ጥያቄ

ልንሠራ የፈለግነውን ሥራ ለምን አስቀድሞ ማቀድ አስፈለገ? ተወያዩበት።

በአንድ ሥራ ላይ ማቀድ የሚከተሉትን ጥቀሞች ያስገኛል።

1. ልከናወን ያለበትን አንድን ሥራ በአግባቡ አንድከናወን ያስችላል።
2. መከናወን ያለባቸውን ተግባሮች በቅደም ተከተል ለማከናወን ይረዳል።
3. ጊዜያችን ከፋፍለን በአግባቡ እንዲንጠቀም ይረዳል።

ተግባር 2.3 የሚከተለውን ሠንጠረዥ በመጠቀም የአንድ ቀን እቅድ አዘጋጁ።

| መከናወን ያለባቸው ሥራዎች ቅደም ተከተል | መከናወን ያለበቸው ሥራዎች | ሥራው የሚከናወንበት ሰአት |
|---|---|---|
| | ከእንቅልፍ መነሳት | |
| | ትምህርት ቤት መሄድ | |
| | የክፍል ትምህርትን መከታተል /ማጥናት/ | |
| | ቤተሰብን መርዳት | |
| | መጫወት | |

ህፃናት እንደ አንድ የህብረተሰብ አካል በተለያዩ የሕብረተሰብ ጉዳዩች ውስጥ

በማቀድ የአቅማቸውን ያህል መሳተፍ አለባቸው።

ለምሳሌ፡ በተለያዩ ክበባት ውስጥ በመሳተፍ፡-

- የጎርፍ መውረጃ ቦይ ማዘጋጀት
- የቆሻሻ መጣያ ቦታ ማዘጋጀት
- በችግኝ ተከላ ላይ መሳተፍ።



*ሥዕል 2.8 ተማሪዎች በክበባት ያቀዱትን ሲያከናውኑ*

የውይይት ጥያቄዎች

በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ምን ምን ክበባት አሉ? ማቋቋም በሚትፈልጉት ክበብ ላይ ተወያዩ።

*መልመጃ* **2.5**

ሀ**.** የሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ።

1. እቅድ ለወደ ፊት ልንሠራ የፈለግነውን ሥራ ያሳያል።
2. እቅድ የተለያዩ ተግባራት የሚከናወኑበትን ቅደም ተከተል ያሳያል።
3. ለተማሪዎች የዕለት ተዕለት እቅድ አያስፈልግም።

ለ**.** ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጥ/ጪ።

1. ከእቅድ ጥቅሞች ውስጥ ሁለቱን ጥቀስ/ሺ።
2. አንድን የትምህርት ቀን በመውሰድ ከጧት እስከ ማታ ማከናወን ያለባችሁን ተግባራት በሰአት ቅደም ተከተል በማከፋፈል የግላችሁን እቅድ አዘጋጁ።

# 2.3. *ለህብረተሰባችን ጉልበት ያስፈልጋል*

የውይይት ጥያቄ

ጉልበት ምንድንው? ጉልበት ለምን ያስፈልጋል? በአካባቢያችሁ የሚታወቁትን የጉልበት ምንጮች በዝርዝር ከጻፋችሁ በኋላ ተወያዩበት።

## ጉልበት ለኅብረተሰቡ ያለው ጥቅም

**1.**  ጉልበት ምግብን ለማብሰል ይረዳል

ሥዕል 2.9 ከማገዶ በሚገኘው ጉልበት ምግብን ማብሰል

## 2. ከጉልበት ብርሃን እናገኛለን



ሥዕል 2.1 0 ከኤሌክትሪክ ጉልበት ማግኘት

## 3. ጉልበት የተለያዩ ማሽኖችን ለማንቀሳቀስ ይረዳል



ሥዕል 2.11 ጉልበት ማሽኖችን ሲያንቀሳቅስ

**4.** ጉልበት ምግብ እንዲናዘጋጅ ይረዳናል



*ሥዕል 2.12* ጉልበት በቤት ውስጥ ምግብ ለማዘጋጀት

## **5.** ጉልበት ለተለያዩ መጓጓዣዎች ይጠቅማል

ለምሳሌ መኪና፣ መርከብ፣ አውሮኘላንና ባቡር በነዳጅ ጉልበት ይንቀሳቀሳሉ።







ባቡር መኪና





መርከብ አውሮኘላን

*ሥዕል 2.13 ጉልበት ለመጓጓዣ /ለትራንስፖርት/ ይጠቅማል*

## የጉልበት ምንጮች

በአካባቢያችሁ ጉልበት ከምን ይገኛል?

የጉልበት ምንጮችን በሦስት በመክፈል ማየት እንችላለን።

እነርሱም፣

**1.** ከአካባቢ የሚገኙ የጉልበት ምንጮች

ማለት ማገዶ፣ ከሰል፣ ኩበት፣ ገለባ የመሳሰሉት ናቸው።

ከአካባቢ የሚገኙ የጉልበት ምንጮች






ሥዕል *2.14* ጉልበት ከእንጨትና ከኩቦት ይገኛል

## 2. ነዳጅ

ነዳጅ የሚባሉት እንደ ፔትሮሊየም፣ የተፈጥሮ ጋስና የድንጋይ ከሰል ያሉ ናቸው።



ሥዕል *2.15* የድንጋይ ከሰል ጉልበት




ሥዕል *2.16* ፔትሮሊየም

## 3. የተፈጥሮ የጉልበት ምንጮች:

እነዚህም፥ ፀሐይ፣ ንፋስ፣ ወራጅ ውሃና ከመሬት የሚወጣ እንፋሎት የመሳሰሉትን በውስጡ ይይዛል።



ሥዕል *2.17* ከመሬት የሚወጣ እንፋሎት



ሥዕል *2.18* የንፋስ ጉልበት

መልመጃ **2.6**

**ሀ.** ከሚከተሉት ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ።

1. መኪና አውሮፕላንና መርከብ የምንቀሳቀሱበትን ጉልበት ለማግኘት ምን ይጠቀማሉ?

ሀ. ንፋስ ሐ. እንጨት

ለ. የተፈጥሮ ጋስ መ. የነዳጅ ዘይት.

2. ኃይል ለምን ይጠቅማል?

ሀ. ለመንገዣ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

ለ. ምግብ ለማብሰል

ሐ. ብርሃን ለመስጠት

3. ከሚከተሉት የጉልበት ምንጮች ውስጥ ልዩ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. የፀሐይ ሙቀት ሐ. የብርሃን ጉልበት

ለ. ወራጅ ውሃ መ. ንፋስ

4. ከሚከተሉት ውስጥ በሁሉም ቦታ የሚገኝ የጉልበት ምንጭ የቱ ነው?

ሀ. መራጅ ውሃ ሐ. ቤንዝንና ናፍጣ

ለ. ንፋስ መ. ሁሉም

**ለ.** ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጥ/ጪ።

1. ጉልበት ከሚሰጠው ጥቅሞች ውስጥ ሦስቱን ጥቀስ/ሺ።
2. ሕብረተሰባችን ከሚጠቀምባቸው ባህላዊ የጉልበት ምንጮች ውስጥ ሦስቱን ጥቀስ/ሺ።

**2.4**ነገሮችን ከሸክላ፣ ከለስላሳ ኘላስቲክና ከወረቀት መሥራት

የዚህ ትምህርት ርዕስ ነገሮችና ሞዴሎችን ከማዘጋጀት ጋር ይያያዛል። ሞዴል ምንድ ነው?

ሞዴል ማለት በተጨባጭ በምድር ላይ የሚገኝ የአንድ ነገር ወካይ ነው። ሞዴልን ከሸክላ፣ ከለስላሳ ኘላስትኮች፣ ከካርቶንና ከተለያዩ ወረቀቶች ማዘጋጀት ይቻላል።

እንደ ሙጫ፣ እሾክ፣ ሙቅ እና የመሳሰሉት የተለያዩ የሞዴል ክፍሎችን ለማያያዝ ይረዳል።

የሞዴል ንድፍ ማዘጋጀት

የሞዴልን ንድፍ ሲናዘጋጅ ትኩረት ሊንሰጣቸው የሚገቡ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው። በአካባቢያችን ከሚገኙ ነገሮች ውስጥ በቅድሚያ የትኛውን ሞዴል መሥራት እንዳለብን ለይተን ማወቅ ይኖርብናል።

ለምሳሌ

- የውሃ እንስራ ሞዴል
- የመኖሪያ ቤት ሞዴል
- የሲኒ ሞዴል
- የጀበና ሞዴል የመሳሰሉት ናቸው።

ሞዴል የሚሠራላቸው ነገሮች አካልና ሁኔታን ለይቶ ማወቅ

ለምሳሌ፡ የእንስራ ሞዴል የሚንሠራ ከሆነ የእንስራ ቅርጽ ምን እንደሚመስል ለምሳሌ አፋን፣ አንገቱን፣ ስፋቱንና ጆሮዎቹን ማስታወስ ማለት ነው።

**የሞዴሎችን ንድፍ ውበት መንደፍ/ መቀየስ/**

- ሞዴሉን ልንሠራ የፈለግነውን ነገር ሥዕሉን ማንሳት
- የተለያዩ ውበት ያላቸውን ነገሮች ሞዴሎችን ማዘጋጀት

ለምሳሌ፡

የእንስራ ሞዴል

የእንስራ አፍ ውበት

የእንስራ ስፋት ውበት

የእንስራ ጆሮ ውበት ናቸው።

ተግባር **2.5**

በአካባቢያችሁ ከሚገኙ እንደ ለስላሳ ኘለስቲክ፣ ካርቶን፣ ጭቃና ወረቀት በመጠቀም በግላችሁ አንዳንድ ሞዴል በመሥራት ለመምህራችሁ አሳዩ።

## መልመጃ **2.7**

ሀ**.** ለሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ትክክለኛ መልስ ምረጥ/ጪ።

1. ለአንድ በምድር ላይ የሚገኝ ተጨባጭ ነገር ወካይ ምን ይባላል?

ሀ. ጭቃ　　　　　　　　　　ሐ. ወረቀት

ለ. ሞዴል　　　　　　　　　　መ. ሙጫ

2. ከሚከተሉት ዕቃዎች ውስጥ ከሸክላ የሚሠራ የቱ ነው?

ሀ. ኳስ

ለ. እንስራ

ሐ. ጫማ

መ. ልብስ

3. ከሚከተሉት ነገሮች ውስጥ አንዱ ሞዴልን ለመሥራት ያገለግላል፡፡

ሀ. ሸክላ ሐ. ካርቶን

ለ. ጭቃ መ. ሁሉም

ለ. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ትክክል የሆነውን ሃሳብ እውነት ትክክልኛ ያልሆነውን ሃሳብ ሀሰት በማለት መልስ/ሺ፡፡

1. እንሥራን ከሸክላ መሥራት ይቻላል፡፡
2. የሲኒ ሞዴል ለመሥራት በቅድሚያ የእንስራ ሞዴል እንዴት እንደሚሠራ ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡
3. እንሥራ ጆሮ እንጂ አፍ የለውም፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# ተፈጥሮአዊ አካባቢያችን

## 3.1 ተፈጥሮአዊ ክስተቶች

የውይይት ጥያቄዎች

በአካባቢያችሁ የሚታዩ ተፈጥሮአዊ ክስተቶችን በመጠየቅ በክፍላችሁ ውስጥ ተወያዩበት።

በየዕለቱ በአካባቢያችን የተለያዩ ክስተቶች ይታያሉ። የሚታዩትም ነገሮች አንደ ጨለማ /ሌሊት/፣ ቀን፣ በጋ፣ ክረምት ፀደይ፣ በልግ፣ ድርቅ፣ ጐርፍ፣ ቀስተ ደመና፣መወለድ፣ ማደግ፣ መሞት፣ ንፋስ እና ብርሐን የመሣሰሉትን አስተውላችሁ ታውቃላችሁ; እነዚህ ነገሮች ተፈጥሮአዊ ክስተቶች ይባላሉ።
ተፈጥሮአዊ ክስተቶች በመፈራረቅ እና አልፎ አልፎ ይከሠታሉ። በመፈራረቅ ከሚፈጠሩ ክስተቶች ቀን፣ ሌሊትና ወቅቶችን መጥቀስ ይቻላል። አልፎ አልፎ በድንገት ከሚፈጠሩ ክስተቶች ደግሞ ጐርፍ፣ ድርቅ፣ ቀስተ ደመና የመሣሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።

### ቀንና ሌሊት

ብርሃንና ጨለማን ታውቃላችሁ? የብርሃን ጊዜ ምን ይባላል? የጨለማ ጊዜስ?

ፀሐይ ወጥታ እስከምትጠልቅ /የብርሃን/፣ ፀሐይ ጠልቃ እስከምትወጣ /የጨለማ/ ያለው ጊዜ በአንድ ላይ አንድ ቀን ይባላል። ፀሐይ ወጥታ እስከምትጠልቅ ያለው ጊዜ ቀን ይባላል።

ፀሐይ ጠልቃ ተመልሳ እስክምትወጣ ያለው ጊዜ ደግሞ ሌሊት ይባላል።

ሌሊት የጨለማ የብርድ ጊዜ ነው።

አንድ ቀን በተለያዩ ጊዜያት ይከፈላል። እነርሱም ጠዋት፣

እኩለ ቀን፣ ቀትር፣ ማታና እኩለ ሌሊት የመሳሰሉትን በውስጡ ይይዛል። በእናንተ አካባቢ የሚታውቁት ሌላ ነገር ካለ ተናገሩ።



*ሥዕል 3.1 ማለዳ/ጠዋት*



ሥዕል

3.2 ማታ

## መልመጃ 3.1

በቅንፉ ውስጥ ከተፃፉት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ በማስመር መልስ/ሺ።

1. ፀሐይ የምትወጣበት ጊዜ ( ማታ/ ጠዋት)
2. ከፍተኛ ሙቀት የሚሰጥ (ፀሐይ/ጨረቃ)
3. በማታ ጊዜ ብርሃን የሚሰጥ (ፀሐይ/ጨረቃ)
4. ምሣ የሚበላበት ሰዓት ( ምሽት/ቀትር )

### ወቅቶች

ከተፈጥሮ ክስተቶች ውስጥ አንዱ ወቅቶች ነው። ወቅቶች በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል። እነርሱም፣ ክረምት፣ ፀደይ፣ በጋና በልግ ናቸው።

የውይይት ጥያቄ

ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመወያየት መልሱ።

ሀ . ዝናብ የሚዘንብበት ወቅት ምን ይባላል?

ለ. በክረምትና በጋ መካከል ያለው ወቅት ምን ይባላል?

ሐ. አንድ ወቅት ስንት ወራት በውስጡ ይይዛል?

መ. ትምህርት ቤት በምን ወቅት ይዘጋል?

ሠንጠረዥ 3.1 በይበልጥ በኦሮሚያ ውስጥ የሚገኝ ወቅት

| ወቅት | ወራት | የሚከናወኑ የእርሻ ተግባራት |
|---|---|---|
| ክረምት /የዝናብ ጊዜ/ | ሰኔ<br>ሐምሌ<br>ነሐሴ | እህል መዝራት<br>ችግኝ መትከል<br>አረም ማረም |
| ፀደይ /ዝናብ የሚያባራበት ጊዜ/ | መስከረም<br>ጥቅምት<br>ህዳር | ማረም<br>አዝመራ/አጨዳ/ |
| በጋ /የሙቀት ጊዜ/ | ታህሣሥ<br>ጥር<br>የካቲት | ምርት መሰብሰብ፣ ውቂያ |
| በልግ /ዝናብ አልፎ አልፎ የሚዘንብበት ጊዜ/ | መጋቢት<br>ሚያዝያ<br>ግንቦት | አንዳንድ የእህል<br>አይነቶችን መዝራት<br>መደበኛ እርሻ መጀመር |


ከዚህ በላይ ያለውን ሠንጠረዥ እንደ ምሳሌ በመውሰድ ከመኖሪያ አካባቢያችሁ ሁኔታ ጋር በማሻሻል በክፍል ውስጥ ከመምህራችሁ/

መምህርታችሁ ጋር ተወያዩበት።

## ቀስተ ዳመና

ስለ ቀስተ ደመና ምን ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ቀስተ ደመናን አይታችሁ ታውቃላችሁ? በቀስተ ደመና ውስጥ የሚታዩት ቀላማት ምን ምን ናቸው?

ቀስተ ደመና የሚፈጠረው የፀሐይ ጨረር በዝናብ ጠብታ ውስጥ ሲያልፍ ነው። በቀስተ ደመና ውስጥ የሚታዩ ቀለማት ሰባት ናቸው። እነርሱም፥ ቀይ፣ ብርቱካናማ፣ ቢጫ፣ አረንጓዴ፣ ሰማያዊ፣ ወይን ጠጅና ሐመራዊ ና ናቸው።



*ሥዕል 3.4 ቀስተ ደመና*

**ድርቅ**

ድርቅ ምንድነው? በአካባቢያችሁ ድርቅ ተከስቶ ያውቃል? ምን ችግር ያስከትላል? ድርቅ ዝናብ ሲጠፋና በጋ ሲረዝም ሊከሰት የሚችል ተፈጥሮአዊ ክስተት ነው። የዝናብ እጥረት ሲኖር የውሃ እጥረት ይከሰታል። ይህ ችግር በብዛት በቆላማ ቦታዎች ይከሰታል። አልፎ አልፎ በሌሎች ሥፍራዎችም ይከሰታል። ድርቅ ሕይወት ባላቸው ነገሮች ላይ ጉዳት ያደርሳል። ድርቅ በደን መጥፋትና በአየር መዛባት ይመጣል። ስለዚህ በድርቅ አማካይነት የሚመጡ ችግሮችን ለመከላከል ደን አለመመንጠር፣ መንከባከብና ችግኞችን መትከል አስፈላጊ ነው።

ፕሮጀክት **3.1**

በአካባቢያችሁ ወደሚገኘው የግብርና ባለሙያ በመሄድ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከጠየቃችሁ በኋላ የሚሰጣችሁን መልስ በመጻፍ በክፍላችሁ ውስጥ ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

1. ድርቅ የሚያስከትለው ችግር ምንድነው?
2. ድርቅ እንዳይከሰት የምንከላከልባቸው መንገዶች ምን ምን ናቸው?
3. ከድርቅ የሚያያዙ የተፈጥሮ ክስተቶች ምን ምን ናቸው?
4. ችግኞችን መትከልና መንከባከብ ምን ጥቅም አለው?

**ጎርፍ**

በአካባቢያችሁ ጎርፍ እንዴት ይከሰታል? ጎርፍ ምን ምን ችግሮችን ያስከትላል? ጎርፍን የሚንከላከልባቸው ዘዴዎች ምን ምን ናቸው? ተወያዩበት።

ጎርፍ ከተፈጥሮ ክስተቶች ውስጥ አንዱ ነው። ጎርፍ ብዙውን ጊዜ በክረምት ወቅት ከባድ ዝናብ ሲዘንብ ወንዞች ከልክ በላይ ሞልተው ሲፈሱ ይከሰታል።

ጎርፍ በንብረትና ሕይወት ባላቸው ነገሮች ላይ ጉዳት ያደርሳል። ጎርፍን ለመከላከል ችግኞችን መትከልና መንከባከብ እንዲሁም ጎርፍ የሚሄድበትን ቦይ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው።



*ሥዕል 3.5 ጎርፍ*

## የሕይወት ደረጃዎች

የውይይት ጥያቄ

ሕይወት ያላቸው ነገሮች በምን ምን የሕይወት ደረጃዎች ውስጥ ያልፋሉ?

በአካባቢያችሁ በቅርብ ቀን የተወለደ/ች ሕፃን ታስታውሳላችሁ? የሞተ ሰውስ አለ?

ሕይወት ያላቸው ነገሮች የሚያልፉበት የሕይወት ደረጃዎች መወለድ፣ ማደግና መሞት ናቸው። እንስሳት እና እጽዋት ሁሉ በዚህ የሕይወት ደረጃዎች ውስጥ ያልፋሉ።

በዚህ ሁኔታ የወባ ትንኝ እና የእፅዋት የሕይወት ደረጃዎችን እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል።

እንቁላል → እጭ → ሙሽሬ → ጉልምስ → መሞት

ዘር → ግንቆላ → ብቅሊት → አበባ → መሞት

### *መልመጃ* **3.2**

ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘ ፊደል ምረጥ/ጪ።

1. በመፈራረቅ የሚፈጠሩ ክስተቶች የትኞቹ ናቸው?

ሀ) ድርቅ ለ) ወቅቶች ሐ) ጐርፍ

2. በበልግ ወቅት የሚመደብ ወር የቱ ነው?

ሀ) መስከረም ለ) ሰኔ ሐ) ሚያዝያ

3. በዝናብ እጥረት የሚፈጠረው ክስተት የቱ ነው?

ሀ) ጎርፍ ለ) ድርቅ ሐ) ቀስተደመና

4. ከተፈጥሮ ክስተቶች ውስጥ የተለያዩ ቀለማት የያዘ የቱ ነው?

ሀ) ድርቅ ለ) ቀስተ ዳመና ሐ) ጎርፍ

5. ከወቅቶች ውስጥ በአካባቢያችሁ ዝናብ በብዛት የሚዘንብበት የቱ ነው?

ሀ) ፀደይ ለ) በልግ ሐ) ክረምት መ) በጋ

ለ. አጭር መልስ ስጥ/ጪ።

1. ሕይወት ያላቸው ነገሮች የሚያልፉባቸውን ሦሥት የሕይወት ደረጃዎችን ግለፅ/ጪ።
2. ድርቅን ለመከላከል ከሚቻልባቸው ዘዴዎች ውስጥ ሁለቱን ጥቀስ/ሽ።
3. ጎርፍ ከሚያስከትለው ጉዳት ውስጥ ሁለቱን ጥቀስ/ሽ።

የመለኪያ መሣሪያዎች

በአካባቢያችሁ ሰዎች ርዝመት፣ መጠነቁስንና ጊዜን በምን በምን ይለካሉ?

ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት።

የመለኪያ መሣሪያዎች በሁለት ቦታ ይመደባሉ። እነርሱም፣

ሀ. ባህላዊ የመለኪያ መሣሪያዎች

ለ. ዘመናዊ የመለኪያ መሣሪያዎች

## ባህላዊ የመለኪያ መሣሪያዎች

### ባህላዊ የርዝመት መለኪያ መሣሪያዎች


በአካባቢያችሁ ባህላዊ የርዝመት መለኪያ መሣሪያዎች ምንምን ናቸው?

በብዙ አካባቢዎች ርዝመትን ለመለካት የሚያገለግሉ ባህላዊ መለኪያዎች አሉ። ከእነዚህ መሳሪያዎች ውስጥ ስንዝር፣ ክንድ፣ ጫማ፣ እርምጃ፣ ገመድና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።






ክንድ




ስንዝር







*ሥዕል* ***3.6*** ባህላዊ የርዝመት መለኪያዎች

ተግባር **3.2**

በክፍል ውስጥ አንድ ጠረጴዛ በመውሰድ አራት የተለያዩ ቁመት ያላቸው ተማሪዎች በክንድና በስንዝር በመለካት ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ ይመዝግቡ።

ሠንጠረዥ **3.3** የተግባር መለኪያ መዝገብ

| ተማሪ | የክንድ መለኪያ ቁጥር | የስንዝር መለኪያ ቁጥር |
|---|---|---|
| ሀ | | |
| ለ | | |
| ሐ | | |
| መ | | |


የውይይት ጥያቄዎች

1. የአራቱም ልኬቶች ውጤታቸው እኩል ነው?
2. ልኬታችሁ ለምን ተለያየ?
3. ባህላዊ የመለኪያ መሣሪያዎች ጉድለት ምን እንደሆነ አውቃችኋል?

4. በአንድ ነገር መለኪያ ላይ የተለያዩ ውጤቶች ቢፈጠሩ የልኬት ውጤቶቹ እንዲመሳሰሉ ምን ማድረግ አለብህ/ሽ?

## ባህላዊ የመጠነ ቁስ መለኪያዎች

በባህላዊ ዘዴ መጠነ ቁስ ሁለት ነገሮችን በማመዛዘን ወይም በማወዳደር ሲለካ ነበር። ከባህላዊ የመጠን ቁስ መለኪያ መሣሪያዎች ቁና፣ እንስራ፣ አቁማዳ፣ ኩባያ፣ ዳውላ፣ እንቅብና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።




አቁማዳ ቁና ኩባያ

*ሥዕል 3.7* ባህላዊ የመጠነ ቁስ መለኪያዎች

## ባህላዊ የጊዜ መለኪያዎች

| ፕሮጀክት **3.2** |
| --- |
| ርዝመቱ ሁለት ሜትር የሚሆን እንጨት በትምህርት ቤታችሁ ግቢ ውስጥ በመትከል የእንጨቱ የጥላ ርዝመት በአንደኛ፣ በሁለተኛ፣ በሦስተኛና በአራተኛ ክፍለ ጊዜያት በመለካት የጥላው ርዝመት መለኪያ ልዩነት ምን ለመለካት እንዲሚረዳ ተገንዘቡ። |

ጥያቄ፡ በባህላዊ ዘዴ ጥላን በመጠቀም ጊዜ እንዴት ይለካል?



ቅትር በኃላ

ሥዕል 3.8 የሰው ጥላ በተለያዩ ጊዜያት

ባህላዊ የርዝመት መለኪያዎች ሁሉ እኩል አይደሉም። ለምሳሌ የርዝመት መለኪያ ክንድ ከሆነ የረጅም ሰው ክንድ ርዝመትና የአጭር ሰው ክንድ ርዝመት እኩል አይደለም። ስለዚህ ሁሉም ሰው የሚያግባባ መለኪያ ዘመናዊ መለኪያ ነው።

## ዘመናዊ መለኪያዎች


ዘመናዊ መለኪያዎች የአንድን ነገር መጠን በትክክልና በተመሳሳይ ሁኔታ ለመግለጽ ይረዳሉ።

## ዘመናዊ የርዝመት መለኪያዎች

ልብስ በምታሰፉበት ጊዜ ልብስ ሰፊው ርዝመታችሁን በምን ይለካል? ዘመናዊ የርዝመት መለኪያዎች ኪሎ ሜትር፣ ሜትር፣ ሴንቲሜትርና ሚሊሜትር የመሳሰሉት ናቸው። ዘመናዊ የርዝመት መለኪያ አሃድ ሜትር ይባላል።

## ተግባር **3.3**


የጠረጴዛ የጐን ርዝመትና ቁመት እንዲሁም የመጽሐፍ ርዝመት መለኪያ የሚገለጽበትን አሃድ በመለየት በክፍል ውስጥ ተወያዩበት።



ሥዕል 3.9 ጠረጴዛና መጽሐፍ

ዘመናዊ የርዝመት መለኪያዎች የርስ በርስ ግንኙነት አላቸው።

1 ኪሎ ሜትር /km/ = 1000 ሜትር/m
1 ሜትር = 1 00 ሰንቲ ሜትር /cm/
1 ሳንቲሜትር = 1 0 ሚሊ ሜትር /mm/






Meetira dadacha’aa



Meetira teephaa

ተታጣ

*ሥዕል 3.1* 0 የሜትር ዓይነቶች

## ዘመናዊ የመጠነ ቁስ መለኪያዎች

በአካባቢያችሁ ሰዎች በሱቅ ውስጥ የሚሸጡትን እቃዎች በምን መሣሪያ ይመዝናሉ? መጠነ ቁስ የሚለካበት መሣሪያ ሚዛን ይባላል። የተለያዩ የመጠነ ቁስ መለኪያዎች ሚዛኖች አሉ። ዘመናዊ የመጠነ ቁስ መለኪያ አሃዶች፡- ኪሎግራም /kg/፣ ግራም /g/፣ ሚሊግራም /mg/ና የመሳሰሉ ናቸው።

| |
|---|
| ዘመናዊ የመጠነ ቁስ አሀዶች ያላቸው ግንኙነቶች<br><br>1 ኪሎ ግራም = 1000 ግራም<br>1 ግራም = 1000 ሚሊግራም ታዋቂ የመጠነ ቁስ አሀድ መለኪያ ኪሎግራም /kg/ ነው |



ሥዕል 3.11 ዘመናዊ የመጠን መለኪያዎች

## ዘመናዊ የጊዜ መለኪያዎች

ዘመናዊ የጊዜ መለኪያ መሣሪያ ሰዓት ይባላል።


የተለያዩ የሰዓት አይነቶች አሉ። እነርሱም የእጅ ሰዓት፣ የግድግዳ ሰዓት፣ የጠረጴዛ ሰዓትና የመሳሰሉት ናቸው።

የሰዓት መለኪያ አሀድ ሴኮንድ፣ ደቂቃ፣ ሰዓት፣ ቀንና ሳምንት የመሳሰሉት ናቸው።


የጊዜ መለኪያ አሀዶች ግንኙነት

| | |
|---|---|
| 60 ሴኮንድ = 1 ደቂቃ | 7 ቀናት = 1 ሣምንት |
| 60 ዳቂቃ = 1 ሰዓት | 30 ቀናት = 1 ወር |
| 24 ሰዓት = 1 ቀን | 365/6 ቀናት = 1 ዓመት |

የጊዜ መቁጠሪያ አሀድ ሴከንድ ይባላል።








የእጅ ሰዓት የጠረጴዛ ሰዓት የግርግዳ ሰዓት

ሥዕል 3.12 የሰዓት አይነቶች

## መልመጃ 3.3

ከዚህ በታች ያሉትን ሰዓቶች በማየት /በማንበብ/ የሚያሳዩትን ጊዜ ተናገር/ሪ።



ሀ ለ ሐ

መ

1. "ሀ" ስንት ሰዓት ያመለክታል;____________
2. "ለ" ስንት ሰዓት ያመለክታል;____________
3. "ሐ" ስንት ሰዓት ያመለክታል;____________
4. የ"መ" ስንት ሰዓት ያመለክታል;____________

ከዚህ በታች ያሉትን ባዶ ቦታዎች ሙላ/ይ።

1. 1 ደቂቃ , ____________ ሴኮንድ
2. 1 ሰዓት , ____________ደቂቃ
3. 1 ቀን , ____________ ሰዓታት
4. 1 ሳምንት , ____________ ቀናት
5. 1 ወር , ____________ ቀናት

# 3.2 *የተፈጥሮ ሀብቶች*

**የውይይት ጥያቄ**

በአካባቢያችሁ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶች ምን ምን እንደሆኑና ጥቅማቸውን በቀበሌያችሁ ውስጥ ያለውን የግብርና ባለሙያ በመጠየቅ በክፍል ውስጥ ተወያዩበት።

የተፈጥሮ ሀብት የሚባሉት አፈር፣ ውሃ ዕፅዋት፣ እንስሳት፣ ማዕድናት፣ ድንጋይ፣ ድንጋይ ከሰል፣ ፔትሮሊየም የመሳሰሉት ናቸው።

በአካባቢያችን የሚገኙት የተፈጥሮ ሀብቶችን ሁለት ቦታ ከፍለን ማየት እንችላለን። እነርሱም፣

1. ሕይወት ያላቸውና

2. ሕይወት የሌላቸው ናቸው

| |
|---|
| **የውይይት ጥያቄ፡**<br>ከላይ የተዘረዘሩ የተፈጥሮ ሐብት አይነቶችን ሕይወት ያላቸውና ሕይወት የሌላቸው ሥር በመመደብ በሁለቱ መካከል ባለው ልዩነት ላይ ተወያዩ። |

## አፈር

የውይይት ጥያቄ

አፈር እንዴት ይፈጠራል? በአካባቢያችሁ የሚገኙት የአፈር አይነቶች ምን ምን ናቸው? በአካባቢያችሁ የሚገኙትን የአፈር አይነት ናሙናዎችን ወደ ክፍል በማምጣት ተወያዩበት።

አፈር ከተፈጥሮ ሀብቶች ውስጥ  አንድ ነው። የተለያዩ የአፈር አይነቶች አሉ። እነርሱም የሸክላ አፈር፣ የአሸዋ አፈርና የለም አፈር ናቸው።

የአፈር ጥቅም

የውይይት ጥያቄ

አፈር ለምን ይጠቅማል? አፈር ለዕፀዋት በሚሰጠው ጥቅም ላይ ተወያዩበት።

የአፈር ጥቅሞች

- ዕጽዋት ከአፈር ውስጥ ውሃና የተለያዩ ማዕድናትን ያገኛሉ።
- አፈር የእፅዋትን ሥር ደግፎ ይይዛል።
- አፈር የጥቃቅን ነፍሳት መኖሪያ ነው።
- አፈር የቤት ቁሳቁሶችን ለመሥራት ያገለግላል። ለምሳሌ ምጣድ፣ እንስራ፣ ማሠሮ የመሳሰሉት ናቸው።
- አፈር የግንባታ መሣሪያዎችን ለማምረት ያገለግላል።
- አፈር የተለያዩ ሞዴሎችን ለመሥራት ያገለግላል።





ሲኒ እንስራ

ድስት

ፈር የሚሠሩ ቁሳቁሶች

በአካባቢያችሁ ከአፈር የሚሠሩ ሌሎች የቤት ቁሳቁሶችን ዘርዝሯቸው።

የአፈር እንክብካቤ

የውይይት ጥያቄ

አፈርን መንከባከብ ለምን ይጠቅማል? አፈርን መንከባከብ እንዴት ይቻላል?


በቡድን ተወያዩበት። አፈር የተለያዩ ጥቅም ስላለው መጠበቅ አለበት።

አፈርን በሚከተሉት ዘዴዎች በመጠቀም መንከባከብ ይቻላል።

- አቀበታማ መሬትን ወደ ጐን በማረስ
- በገላጣ መሬት ላይ ችግኞችን በመትከል
- ጎርፍ የሚፈጠርበትን ቦታ መገደብ /እርከን መሥራት/
- በእርሻ መሬት /ማሣ/ ላይ የተለያዩ እህሎች አፈራርቆ መዝራትና የመሳሰሉት ናቸው።

## የእርከን ጥቅም


- የአፈር መታጠብን ይቀንሳል።
- የዝናብ ወሃ መሬት ውስጥ በመግባት የአፈር እርጥበት እንዲጠበቅ ያደርጋል።
- የውሃ ምንጭ እንዲጎለብት ያደርጋል።



ሥዕል *3.14* እርከን



ሥዕል *3:15* ችግኝ ተከላ



*ሥዕል 3.16 አግድም ማረስ*

### መልመጃ **3.4**

በቡድን በመሆን ከላይ በተገለጹት ዘዴዎች አፈርን በመንከባከብ መጠቀም እንዴት እንደሚቻል በመወያየት ለክፍል ዘገባ አቅርቡ።

## ውሃ


በመኖሪያ ቤታችሁ ውስጥ የምትጠቀሙትን ውሃ ከየት ታገኛላችሁ?

## የውሃ ምንጮች


ውሃ ከምንጭ፣ ከሐይቅ፣ ከወንዝ፣ ከጉድጓድ፣ ከቧንቧ፣ ከዝናብና ከመሳሰሉት እናገኛለን።








የጉድጓድ ውሃ                    የቧንቧ ውሃ



ምንጭ



ዝናብ

*ሥዕል 3: 17 የውሃ ምንጮች*

## የውሃ ጥቅም

የውይይት ጥያቄዎች

የውሃ ጥቅሞችን በመዘርዘር ለክፍል አቅርቡና ተወያዩበት።

ውሃ፡- ለእፅዋት እድገት፣ ለንጽህና፣ ለመጠጥ፣ ለማጓጓዣ፣ በፋብሪካ ውስጥ የተለያዩ ምርቶችን ለማምረት፣ የጉልበትና የብርሃን ምንጭ በመሆን፣ ለአንዳንድ እንስሳ የመኖሪያ ቦታና የመሳሰሉት በመሆን ያገለግላል።




*ሥዕል 3: 18 የውሃ ጥቅሞች*

## ፕሮጀክት **3.3**

ውሃ ለእጽዋት ያለውን ጥቅም መገንዘብ

የፕሮጀክት ሂደት

ሁለት ችግኞችን በመትከል አንዱን ውሃ በማጠጣት ተንከባክቡት፤ ሌላውን ዳግሞ ውሃ ሳታጠጡ ብትቆዩ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በሁለቱ ችግኞች መካከል የሚታየውን ልዩነት ተገነዘቡ።



*ውሃ ያገኘ ችግኝ*



*ውሃ ያጣ ችግኝ*

*ሥዕል 3.19 ውሃ ያገኘ ችግኝና ውሃ ያጣ ችግኝ*

### ውሃን በንጽህና መያዝ

በአካባቢያችሁ ውሃ እንዴት በንጽህና ይያዛል? የውሃን ንጽህና ካልጠበቅህ/ሽ ምን ችግር ያስከትላል? ተወያዩበት።

በአካባቢያችን ያለ ውሃ በተለያዩ ምክንያቶች ሊበከልና ሊባክን ይችላል። ጥራጊ፣ ጥምብና የተለያዩ ቆሻሻዎችን ውሃ ውስጥ መጣል፣ የፋብሪካ ቆሻሻና ዝቃጭ እንዲሁም የሽንት ቤት ፍሳሽን ወደ ውሃ ማፍሰስ ለውሃ መበከል መንስኤ ይሆናሉ።

የተበከለ ውሃ በሰውና ሕይወት ባላቸው ነገሮች ላይ ጉዳት ያደርሳል። ስለዚህ ውሃን መንከባከብና ንጽህናውን በመጠበቅ በቁጠባ መጠቀም አስፈላጊ ነው።





ቆሻሻን ወንዝ ውስጥ መጨመር          ወንዝ ዳር መጸዳዳት

ሥዕል **3.2** ዐ ውሃን የሚበክሉ ነገሮች

የውሃ ንጽህናን ለመጠበቅ የሚከተሉትን ማድረግ አስፈላጊ ነው።

- ብስባሽንና የተለያዩ ቆሻሻዎችን ውሃ ውስጥ አለመጣል
- ከመኖሪያ ቤት፣ ከፋብሪካ፣ ከትምህርት ቤትና ከተለያዩ መሥሪያ ቤቶች የሚወገዱትን ቆሻሻዎች ወደ ውሃ አለመጨመር
- ውሃን አፍልቶ መጠቀም
- ውሃን በንጹህ እቃ መቅዳትና መጠቀም።

## ደን

### የደን ጥቅም

ስለ ደን ጥቅም በቀበሌያችሁ ያለውን የግብርና ባለሙያ ጠይቃችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ዘገባ በማቅረብ ተወያዩበት።





*ሥዕል 3.22 የተፈጥሮ ደን*

የውይይት ጥያቄዎች

ሰው ለምን ደን ይመነጥራል?

- ለእርሻ መሬት ማስፋፊያ
- ለተለያዩ ግንባታዎች የሚውል እንጨት ለማግኘት
- ለማገዶ
- ከተማን ለማስፋፋት
- ለመንገድ ሥራና የመሳሰሉት



*ሥዕል 3.23 የተመነጠረ ደን*

## የደን እንክብካቤ

ደንን አለመመንጠር፣ ዛፎችን በመትከልና ዛፎች የተቆረጡበት ቦታ ላይ መልሶ በማልማትና በመሳሰሉት ዘዴዎች ደንን መንከባከብ ይቻላል።

| ፕሮጀክት 3.4 |
|---|
| በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ባዶ ቦታን በመፈለግ በክፍላችሁ ስም ችግኞችን በመትከል ተንከባከቡ። |

## የደን ጥቅም

- የእንስሳት ምግብና መጠለያ በመሆን
- የንፁህ አየር ምንጭ በመሆን
- ለቤት ቁሳቁሶችና ለቤት መሥሪያ
- ለመድኃኒት ቅመማ
- የቱሪስት መስህብ በመሆን ገቢ ለማስገኘት
- ዝናብን ለመሳብና ለመሳሰሉት ይጠቅማል።

## አየር

### የአየር ጥቅም


የአየር ጥቅም ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? አንደኛ ክፍል የተማራችሁትን በማስታወስ ተወያዩበት።

ተግባር **3.5**

የአየርን ጥቅም ለመረዳት ለአጭር ጊዜ አፍና አፉንጫችሁን አፍኑ። ምን እንደተሰማችሁ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ። ሕይወት ያላቸው ነገሮች ለመኖር አየር ያስፈልጋቸዋል። አየር ለመተንፈስ የሚያገለግል ጋስ በውስጡ ይይዛል። አየር በተለያዩ ነገሮች ሊበከል ይችላል። ለምሳሌ፤

- ከአካባቢ በሚነሳ አቧራ
- ከቤት በሚወጣ ጢስ
- ከመኪናና ከፋብሪካ በሚወጣ ጢስ ይበከላል።





ሥዕል ***3.24*** ከቤት የሚወጣ ጢስ ሥዕል ***3:25*** ከመኪና የሚወጣ ጢስ



ሥዕል 3.26 ከፋብሪካ የሚወጣ ጢስ

| ፕሮጀክት 3.5 |
| --- |
| በመምህራችሁ አማካይነት በአካባቢያችሁ ጉዳት እየደረሰባቸው የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን ምረጡና ጉብኝት አድርጉ። ለምሳሌ የተበከለ ውሃ፣ የተጨፈጨፈ ደን፣ በጎርፍ የተሸረሸረ መሬትና የመሳሰሉት። ይህ ጉዳት የደረሰበትን የተፈጥሮ ሀብት ከጐበኛችሁ በኃላ በምን ምክንያት ጉዳት እንደደረሰበትና በምን ዘዴ እንደምንከባከብ በክፍላችሁ ውስጥ ተወያዩበት። |

## መልመጃ 3.5

ሀ. ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ።

1. ለአየር መበከል ምክንየት የሚሆነው የቱ ነው?

ሀ. የመኪና ጢስ ሐ. የፋብሪካ ጢስ

ለ. የቤት ጢስ መ. ሁሉም መልስ ነው

2. የደን ጥቅም ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ለቤት መሥሪያ ሐ. ለንፁህ አየር ምንጭነት

ለ. ለእንስሳት መጠለያ መ. ለአየር መበከል ምክንያት መሆን

3. የአፈር መሸርሸርን ለመከላከል የሚጠቅመው ዘዴ የቱ ነው?

ሀ. ችግኝ መትከል ሐ. አግድም ማረስ

ለ. እርከን መሥራት መ. ሁሉም መልስ ናቸው

4. የውሃ ጥቅም ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. አፈርን መሸርሸር ሐ. ንጽህናን ለመጠበቅ

ለ. ምግብን ለማብሰል መ. ለመጠጥ

5. የውሃ መገኛ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ዝናብ ሐ. ጓድጓድ

ለ. ሐይቅ መ. መልሱ አልተሰጠም

6. የአፈር ጥቅም የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ለማዕድን መገኛ ሐ. ለነፍሳት መኖሪያ

ለ. ለመኖሪያ ቤት መሥሪያ     መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

**ለ.** ትክክለኛ መልስ ስጥ/ጪ።


1. የአፈር መሸርሸር ከምንከላከልበት ዘዴዎች ውስጥ ሦስቱን ጥቀስ/ሺ።
2. ደን ከሚሰጠው ጥቅሞች ውስጥ ሦስቱን ጥቀስ/ሺ።
3. ከአፈር ከሚሠሩ የቤት ቁሳቁሶች ውስጥ ሦስቱን ጥቀስ/ሺ።
4. ሰዎች ደን የሚመነጥሩበትን ሦስት ምክንያቶች ግለጽ/ጪ።

# 3.3 የአካባቢያችን እጽዋቶች

ተግበር **3.6**

በአካባቢያችሁ የሚገኙትን የተለያዩ እጽዋቶች በመሰብሰብ ወደ ክፍላችሁ አምጡ። የተሰበሰቡትን የእጸዋት አካላት አንድ በአንድ በመለየት አንዳችሁ ለአንዳችሁ አሳዩ።

የእያንዳንዱ የእፅዋት አካል ተግባር ላይም ተወያዩበት።




*ሥዕል* ***3:27*** *የእጽዋት አካላት*

### የእፅዋት አካላትና ተግባራቸው

የእጽዋት አካላት ሥር፣ ግንድ፣ አበባና ቅጠል ናቸው።

### የእጸዋት አካላት ተግባር

**ሥር፡-** ውሃንና ማዕድናትን ከአፈር ውስጥ መምጠጥና እፅዋቱ ጠንክሮ እንዲቆም ጥንካሬ ይሰጠዋል።

ግንድ፡ እፅዋቱ እንዲቆም፣ ምግብ፣ ውሃ እንዲሁም ማዕድናትን ከሥር ወደ ተለያዩ የእፅዋት አካላት ለማስተላለፍ ይረዳል።

ቅጠል፡ የእፅዋቱን ምግብ የሚያዘጋጅ አካል ነው።.

አበባ፡ በአበባ ለሚራቡ እፅዋቶች የመራቢያ አካል ነው። ለአንዳንድ ነፍሳት ደግሞ እንደ ምግብ ምንጭ ያገለግላል። ለምሳሌ፡- ንብና ቢራቢሮ። አበባ ለአካባቢ ውበትም ያገለግላል።

ተግባር **3.7**

የተለያዩ አበባዎችን ወደ ክፍል በማምጣት ቀለማቸውንና ቅርፃቸውን ተመልከቱ። የተለያዩ እፅዋቶች የተለያየ ቀለማት ያላቸው አበባ አላቸው። ለምሳሌ፡ ቀይ፣ ቢጫ፣ ነጭና የመሳሰሉት።

| |
|---|
| ኘሮጀክት **3.6** ለእጽዋቶች እድገት ምን ምን እንደሚያስፈልጋቸው የቀበሌያችሁን የግብርና ባለሙያ በመጠየቅ ለክፍላችሁ ዘገባ በማድረግ ተወያዩበት። |

### *መልመጃ* **3.6**

በ "ለ" ረድፍ የተዘረዘሩትን ከ"ሀ" ረድፍ ጋር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምድ/ጂ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ውሃንና ማዕድናትን ለመምጠጥ ይረዳል | ሀ. ግንድ |
| 2. ለመራቢያ ይረዳል | ለ. ሥር |
| 3. ምግብ ለማዘጋጀት ይረዳል | ሐ. አበባ |
| 4. እጽዋትን ደግፎ ለማቆም ይረዳል | መ. ቅጠል |

## *3.4* የአካባቢያችን እንስሳት

የውይይት ጥያቄ

በአካባቢያችሁ ከሚገኙ እንስሳት ውስጥ የምታውቋቸውን ዘርዝሩ።


በአካባቢያችሁ ያሉትን የግብርና ባለሙያ በመጠየቅ እንስሳትን በአኗኗር ሁኔታ በአመጋገብ፣ በእንቅስቃሴያቸው፣ በብዛታቸው፣ በመራቢያቸው፣ በአካል ሽፋናቸውና በመሳሰሉት ላይ ዘገባ በማዘጋጀት ከክፍላችሁ ተማሪዎች ጋር ተወያዩበት።

## የእንስሳት አመዳደብ


### ሀ. በመልመድ ባህሪያቸው

እንስሳት በመልመድ ባህሪያቸው በሁለት ይከፈላሉ። እነርሱም የቤት እንስሳትና የዱር እንስሳ ናቸው።


- **የቤት እንስሳት፡** የቤት እንስሳት ለማዳ ሆነው ከሰው ጋር የሚኖሩ ናቸው።



ውሻ




ግመል




በግ



ላም






**አህያ** **ፈረስ**

*ሥዕል 3: 28* የአካባቢያችን የቤት እንስሳት


**የዱር እንስሳት፡** ከሰው ሳይላመዱ በዱር የሚኖሩ ናቸው።






ጉማሬ ቀበሮ





የሜዳ አህያ

አጋዘን






ቀጭኔ









ሥዕል ***3.3*** 0 የዱር እንስሳት

## ለ. በአረባብ ሁኔታቸው


በአረባብ ሁኔታቸው እንስሳት በሁለት ይከፈላሉ። እነርሱም፡


- እንቁላል በመጣል የሚራቡ





ዶሮ እባብ





ዓሣ አዞ

*ሥዕል 3. 3* ዐ እንቁላል በመጣል የሚራቡ

**2.** በመውለድ የሚራቡ እንስሳት








የሌሊት ወፍ

አይጥ

ሰው ነ





ውሻ

ላም

sa'a

*ሥዕል 3 : 31* በመውለድ የሚራቡ እንስሳት

ሐ. በእንቅስቃሴአቸው

እንደ እንቅስቃሴአቸው እንስሳት በሦስት ክፍሎች ይመደባሉ።


**1.** በራሪ እንስሳት




የሌሊት ወፍ

*ሥዕል 3 : 35* በራሪ እንስሳ


**2.** ተሳቢ እንስሳት





እባብ

ዘንዶ እባብ




ቀንድ አውጣ

*ሥዕል 3.34* ተሳቢ እንስሳት

## 3. ተራማጅ እንስሳት




ሰጐን



ዝሆን



ሰው





ጉማሬ


ሥዕል ***3:35*** ተራማጅ እንስሳት

### መ. በአመጋገባቸው

እንስሳት በአመጋገባቸው በሦስት ይከፈላሉ። እነርሱም፣

**1.** እፅዋትን የሚመገቡ እንስሳት





ቀጭኔ ዝሆን







የሜዳ አህያ ጥንቸል ድኩላ

*ሥዕል 3.35* እፅዋትን የሚመገቡ እንስሳት


**2.** *ሥጋ* በል እንስሳት





አንበሣ ነብር





ቀበሮ ጅብ


ሥዕል 3.37 ሥጋ በል እንስሳት

**3.** እጽዋትና ሥጋ በል እንስሳት

ጥያቄ**፡** በአካባቢያችሁ ስላሉት እጽዋትና ሥጋ በል እንስሳት

እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ።





አይጥ ሰው

ሥዕል **3.38** እፅዋትና ሥጋ በል እንስሳት

## ሠ. በአኗኗራቸው

እንስሳት በአኗኗራቸው በሦስት ይከፈላሉ። እነርሱም፣

1. በመሬት ላይ የሚኖሩ እንስሳት



ዝሆን አህያ e ሰጐን i

*ሥዕል 3.38* በመሬት ላይ የሚኖሩ እንስሳት

## 2. በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት



ዓሣ ጉማሬ

*ሥዕል 3:39* በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት

## 7. በመሬት ላይና በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት



ጉርጥ


እንቁራሪት

*ሥዕል 3: 41* በመሬት ላይና በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት


ረ. በአካል ሽፋናቸው

እንስሳት በአካላቸው ሽፋን የተለያዩ ናቸው። እነርሱም፡-


1. ወፍራም ቆዳ ያላቸው እንስሳት




ዔሊ



ዘንዶ




ዓሣ




አዞ

ሥዕል ***3: 43*** ወፍራም ቆዳ


ለ. ፀጉር ያላቸው እንስሳት



Jaldeessa



Jeedala



Hoolaa

ሥዕል *3: 42* ፀጉር ያላቸው እንስሳት

**3.** ክንፍ ያላቸው እንስሳት






ዝይ

ዳክዬ

ሥዕል 3:45 ክንፍ ያላቸው እንስሳት

## ከእንስሳት ውጤቶች የሚሰሩ መሣሪያዎች






ቦርሣ ዋንጫ





ስልቻ ጫማ







የሌሊት ልብስ ጃኬት

ሥዕል 3.44 ከእንስሳት ውጤቶች የሚሰሩ እቃዎች

የመወያያ ጥያቄ

በአካባቢያችሁ ከእንስሳት ውጤት የሚሠሩ እቃዎችን ለመምህራችሁ ንገሩ።

## የእርሻ እንስሳትን መንከባከብ

እንስሳት ለእርሻ ብዙ አገልግሎት ይሰጣሉ።

ጥያቄ፡ በአካባቢያችሁ ለእርሻ የሚያገለግሉ እንስሳትን ለመምህራችሁ ንገሩ። ለእርሻ እንስሳት ሊደረግላቸው የሚገባ እንክብካቤ ላይ በክፍል ውስጥ ተወያዩበት።

## ለእርሻ እንስሳት ሊደረግ የሚገባ እንክብካቤ

የእርሻ እንስሳት

1. በቂ መኖ ማግኘት አለባቸው። ለምሳሌ፡- ሣር፣ ቅጠል፣ ገለባ፣ የእህል ፋጉሎ፣ ጨውና የመሳሰሉት ናቸው።
2. ከዝናብ፣ ከፀሐይ፣ ከብርድና ጉዳት ሊያስከትሉባቸው ከሚችሉ እንስሳት ሊከልላቸው የሚችል መጠለያ ሊኖራቸው ይገባል።
3. ጤንነታቸው መጠበቅ አለበት። ጥሩ ጤንነት እንዲኖራቸው
   - መኖና ንፁህ ውሃ ማግኘት ይኖርባቸዋል።
   - የአካላቸው ንጽህና መጠበቅ አለበት
   - መጠለያቸው በየጊዜው መጽዳት አለበት
   - ክትባት ማግኘት ይኖርባቸዋል። .
   - የታመሙ እንስሳት በወቅቱ መታከም አለባቸው።

የእርሻ እንሰሳትን ለመንከባከብ የሚያስፈልጉ እቃዎች፡-

1. ገላቸውን ለማጽዳት የሚያገለግል ብሩሽ
2. ውሃ ለማጠጣት የሚያገለግል ገንዳ
3. መኖ ለመስጠት የሚያገለግል እቃ

የመወያያ ጥያቄ

በአካባቢያችሁ የእንስሳትን ገላ ንጽህና ለመጠበቅ የሚያገለግሉ እቃዎች ምን ምን ናቸው; ውሃና መኖን ለእንስሳት ለመስጠት የሚያገለግሉ ምን ምን እንደሆኑና ከምን እንደተሠሩ ቤተሰቦቻችሁን በመጠየቅ ለክፍል አቅርቡ።

## መልመጃ **3.7**

ሀ**.** ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ/ሺ።

1. በመሬት ላይና በውሃ ውስጥ መኖር የሚችል እንስሳ የትኛው ነው?

ሀ. ዓሣ ለ. እንቁራርት ሐ. ዔሊ መ. ቀበሮ

2. እፅዋትና ሥጋ በል ከሆኑት እንስሳት ውስጥ የሚመደብ የቱ ነው?

ሀ. ሰው ለ. ዝንጀሮ ሐ. አይጥ መ. ሁሉም መልስ ነው

3. በመውለድ ከሚራቡት እንስሳት ውስጥ የሚመደብ የቱ ነው?

ሀ. የሌሊት ወፍ ለ. ዳክዬ ሐ. አዞ መ. ዘንዶ

4. እንቁላል በመጣል ከሚራቡት እንስሳት ውስጥ የሚመደብ የቱ ነው?

ሀ. አዞ ለ. እባብ ሐ. ዶሮ መ. ሁሉም መልስ ነው

5. ከበራሪ እንስሳት ውስጥ የሚመደብ የቱ ነው?

ሀ. ሰጐን ለ. ዳክዬ ሐ. ዔሊ መ. ዘንዶ

6. ሥጋ በል እንስሳት ውስጥ የሚመደብ የቱ ነው?

ሀ. አንበሣ ለ. ነብር ሐ. ቀበሮ መ. ሁሉም መልስ ነው

7. እፅዋት በል ብቻ የሆነ እንሰሳ የቱ ነው?

ሀ. ድኩላ ለ. ቀጭኔ ሐ. ጅብ መ. ሀ ና ለ

8. የአካባቢያችን እንስሳት ጥቅም የሆነ የቱ ነው?

ሀ. የምግብ ምንጭ ሐ. ለቤት ቁሳቁስ መሥሪያ

ለ. ልብስ ለማምረት መ. ሁሉም መልስ ነው

ለ**.** ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጥ/ጪ።

1. በመኖሪያ ቦታቸው ላይ በመመርኮዝ የእንስሳትን አመዳደብ ዘርዝር/ሪ።

2. ለሚከተሉት ሁለት ሁለት ምሳሌዎች ስጥ/ጪ።

ሀ. ከሰው ጋር የሚኖሩ እንስሳት።

ለ. እንቁላል የሚጥሉ እንስሳት።

ሐ. እፅዋትና ሥጋ በል እንስሳት።

መ. በመውለድ የሚራቡ እንስሳት።

ሠ. በራሪ እንስሳት።

# ምዕራፍ አራት

# የወረዳችን/ የከተማችን/ መስተዳድር

## 4.1 የወረዳችን /የከተማችን/ መገኛ

የወረዳህ/ሽ /የከተማህ/ሽ/ መስተዳድር ስም ምን ይባላል?


የወረዳህ/ሽ /የከተማህ/ሽ/ መስተዳድር በምን ዞን ውስጥ ይገኛል?

# አራቱ ዋና ዋና አቅጣጫዎች

አቅጣጫ ምንድን ነው?

አንድ ቦታ ከሌላ ቦታ በየት በኩል እንደሚገኝ የሚታወቅበት ሁኔታ አቅጣጫ ይባላል።

ምስራቅ /




ሰሜን

ምዕራብ

ሥዕ

ሥዕል **4.1** አራቱ አቅጣጫዎች

አንድ ሰው ወደ ፀሐይ መውጫ ዞሮ ከቆመ

- የፀሐይ መውጫ ምሥራቅ
- ጀርባው/ዋ ደግሞ ምዕራብ
- ግራ እጁ/ዋ የሰሜን አቅጣጫና
- የቀኝ እጁ/ዋ ደግሞ የደቡብ አቅጣጫን ያመለክታል። ስለዚህ አራቱ ዋና ዋና አቅጣጫዎች ምሥራቅ፣ ምዕራብ፣ ሰሜንና ደቡብ ናቸው። ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን አቅጣጫዎች በክፍል ውስጥ በመቆም ከጓደኞቻችሁ ጋር ተራ በተራ አንዳችሁ ለሌሎቻችሁ አሳዩ።

## መልመጃ 4.1

ሀ. ከዚህ በታች ላሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ሰጥ/ጪ።

1. ትምህርት ቤትህ/ሽ ከመኖሪያ ቤትህ/ሽ በየትኛው አቅጣጫ እንደሚገኝ ቤተሰብህን/ሽን በመጠየቅ ለመምህርህ/ሽ ንገር/ሪ።

2. በትምህርት ቤትህ/ሽ ግቢ ውስጥ በተለያዩ አቅጣጫዎች የሚገኙትን ነገሮች በመለየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ።
3. በአራቱም ዋና ዋና አቅጣጫዎች ወረዳችሁን የሚያዋስኑ ሌሎች ወረዳዎችን ወላጆችህን/ሽን በመጠየቅ ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ ንገር/ሪ።
4. ትምህርት ቤትህን/ሽን የሚያጐራብቱ ዋና ዋና /ታዋቂ/ ቦታዎችን ከነአቅጣጫዎቻቸው ዘርዝር/ሪ።

ለ. ከዚህ በታች ያሉትን ዐረፍተነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ።

1. አንድ ቦታ ከሌላ ቦታ በየት በኩል እንደሚገኝ የሚታወቅበት ሁኔታ አቅጣጫ ይባላል።
2. የአንድን ቦታ መገኛ የሚያሳዩ ዋና ዋና አቅጣጫዎች ሰሜንና ደቡብ ብቻ ናቸው።

ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጥ/ጪ።

1. የፀሐይ መውጫ በየትኛው አቅጣጫ ነው;


   ሀ. ሰሜን ለ. ምሥራቅ ሐ. ምዕራብ መ. ደቡብ

2. ጧት ቀመን ፀሐይን ስንመለከት ጀርባችን የሚያመለክተው የትኛውን አቅጣጫ ነው?

   ሀ. ሰሜን ለ. ምሥራቅ ሐ. ምዕራብ መ. ደቡብ

የወረዳችን /የከተማችን/ አንጻራዊ መገኛ

በአራቱ አቅጣጫ ወረዳችሁን የሚያዋስኑ ወረዳዎችን እርስ በርሳችሁ ተናገሩ። ለአንድ ቦታ ቅርብ ከሚገኙት ቦታዎች ጋር በማነጻጸር አቅጣጫንና የአንድን ቦታ መገኛ የመግለጽ ዘዴ አንጻራዊ መገኛ ይባላል። የወረዳችሁን አንጻራዊ መገኛ ስትገልፁ በአራቱ አቅጣጫዎች ወረዳችሁን የሚያዋስኑትን ሌሎች ወረዳዎችን ለዩ። የከተማችሁን አንጻራዊ መገኛ ስትገልጹ በአራቱ አቅጣጫ ከተማችሁን የሚያዋስኑትን ቀበሌዎች ለዩ። የትምህርት ቤታችሁን መገኛ በንፅፅር ስትገልፁ ትምህርት ቤታችሁን የሚያዋስኑ ቀበሌዎችንና ታዋቂ ቦታዎችን በአራቱም አቅጣጫ ለዩ።



ሥዕል ***4.2*** የአምስት ወረዳዎች ሞዴል ካርታ

ተግባር **4.1**

ሥዕል 4.2 ላይ በመመሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ/ጪ.

**1.** የ"ሀ" ወረዳ በሰሜን ከ---------------------- ወረዳ ጋር ይዋሰናል።

**2.** የሀ ወረዳ በደቡብ ከ ---------------------- ወረዳ ጋር ይዋሰናል።

**3.** የሀ ወረዳ በምሥራቅ ከ-------------------- ወረዳ ጋር ይዋሰናል።

**4.** የሀ ወረዳ በምዕራብ ከ---------------------- ወረዳ ጋር ይዋሰናል።

## መልመጃ **4.2**

ሀ**.** ከዚህ በታች ያሉት ዐረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል

ካልሆኑ ደግሞ ሀሰት በማለት መልስ/ሽ።

1. አንጻራዊ መገኛን ለመግለጽ በቅርበት የሚገኙ ቦታዎች እንጠቀማለን።
2. የትምህርት ቤታችን መገኛ በአንፃራዊ መገኛ መግለጽ ይቻላል።
3. ወረዳችንን በአንፃራዊ መገኛ መግለጽ አይቻልም።

ለ**.** ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጥ/ጪ።

1. አንጻራዊ መገኛ ምንድን ነው;

ሀ. የመሬት አቀማመጥ.

ለ. የአንድ ቦታ መገኛ ከሌሎች ቦታዎች ጋር በማነጻጸር መግለጽ.

ሐ. የአንድ ቦታ ርቀት

መ. የአንድ ቦታ ስፋት

2. የወረዳ አንጻራዊ መገኛን ከምን ጋር አነጻጽረን እንገልጻለን?

ሀ. በአቅራቢያ ከሚገኙት ወረዳዎች ጋር።

ለ. በአቅራቢያ ከሚገኙት ቀበሌዎች ጋር።

ሐ. በአቅራቢያ ከሚገኙት ከተሞች ጋር።

መ. በአካባቢ ከሚገኙት ወንዞች ጋር።

ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጥ/ጪ።

1. ትምህርት ቤትህን/ሽን የሚያዋስኑትን ቀበሌዎች ጥቀስ/ሺ።
2. ወረዳህን/ሽን የሚያዋስኑት የአቅራቢያ ወረዳዎችን ጥቀስ/ሺ።
3. ከተማህ/ሽን የሚያዋስኑ የቀበሌ መስተዳድርን ጻፍ/ፊ።

የወረዳችን /የከተማችን/ ታዋቂ ቦታዎች

ኘሮጀክት **4.1**

1. በወረዳችን /በከተማችን/ ውስጥ የሚገኙት ዋና ዋና ታዋቂ ቦታዎችን የአካባቢ ሽማግሌዎችን ቤተሰቦቻችሁን በመጠየቅ ስማቸውን ዘርዝሩ።
2. የወረዳችሁን /የከተሞቻችሁን ታዋቂ ቦታዎችን በመጐብኘት የጉብኝታችሁን ውጤት ከጓደኞቻችሁ ጋር በክፍል ውስጥ በቡድን ተወያዩበት።
3. ስለታዋቂ ቦታዎች መረጃ በመሰብሰብ አስፈላጊነቱ ላይ በፁሑፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ።
4. የወረዳችሁን /የከተማችሁን/ የድሮ ታሪክ አዛውንቶችን በመጠየቅ ያገኛችሁትን መረጃ እያንዳንዳችሁ ለክፍል አንብቡ።

የታዋቂ ቦታዎችን ታሪክ ለማወቅ አዛውንቶችና በመጽሐፍ መልክ የተቀመጡት ጽሑፎችና የመሳሰሉት እንደምንጭ ያገለግላሉ። የታዋቂ ቦታዎች መረጃ ከዚህ በታች ያሉትን ያቀፈ መሆን አለበት። እነርሱም፥

- የዚያ ታዋቂ ነገር መገኛ ቦታ
- ከዚያ ታዋቂ ቦታ ጋር የተያያዙ ድርጊቶች ለምሳሌ ጦርነት የተካሄደባቸው ወይም ድል የተገኙባቸው ቦታዎች
- የዚያ ታዋቂ ቦታ የተፈፀመ ድርጊት ዘመን
- የዚያ ታዋቂ ቦታ ድርጊት የተፈጸመበት ዘመን የነበረ አስተዳደርና የመሳሰሉት ናቸው።

## መልመጃ 4.3

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ሰጥ/ጪ።

1. በወረዳችሁ /ከተማችሁ/ ውስጥ የሚገኙ ታዋቂ የታሪክ ቦታዎች ምን ምን ናቸው?
2. በወረዳችሁ /በከተማችሁ/ የሚገኙ ታዋቂ የታሪክ ቦታዎች ጥቅም ምን እንደሆነ አብራራ/ሪ።
3. ታዋቂና ታሪካዊ የሆኑ ቦታዎች ከትምህርት ቤታችሁ በምን አቅጣጫ እንደሚገኝ በክፍል ውስጥ ተነጋገሩ።
4. የአንድ አካባቢ ታሪክ በምንዘግብበት ጊዜ ምን ምን መረጃዎችን ማቀፍ አለበት?

# 4.2 የወረዳችን /የከተማችን/ የመሬት አቀማመጥ ሁኔታ

በቡድን በመሆን የመኖሪያ አካባቢዎቻችሁን የመሬት አቀማመጥ በመጐብኘት የተገነዘባችሁትን ለክፍል ዘገባ በማቅረብ ተወያዩበት።

ከመሬት ከፍታዎች የተነሳ በመሬት ገፅታ ላይ የሚታዩ ሁኔታዎች የመሬት አቀማመጥ ይባላል። የአንድ አካባቢ የመሬት አቀማመጥ ከፍተኛ፣ ዝቅተኛ፣ ሸለቋማና የመሳሰሉትን ይይዛል።


### የመሬት አቀማመጥ አይነቶች

የመሬት አቀማመጥ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

እነርሱም፣

- ከፍተኛ ቦታ
- ዝቅተኛ ቦታ እና
- ሸለቋማ ቦታ ናቸው

ከፍተኛ ቦታ



ሥዕል 4.3 ከፍተኛ ቦታ.

የከፍተኛ ቦታ አካባቢ የሚባሉት፣ ኮረብታዎች፣ ተራራ ፕላቶና የመሳሰሉት

ናቸው፡፡

ኮረብታ፡ በአንድ አካባቢ ከፍታ ያለው የመሬት አቀማመጥ ነው፡፡




ሥዕል 4.4 ኮረብታ

ፕላቶ፡ ከፍታ ያለውና አናቱ እንደ ጠረጴዛ ዝርግ የሆነ የመሬት አቀማመጥ ነው፡፡



ሥዕል 4.5 ፕላቶ

ተራራ፡ ተራራ በአንድ አካባቢ ወደ ላይ በጣም ርዝመት ያለውና ከፍ ብሎ የሚታይ የመሬት አቀማመጥ ነው፡፡



ሥዕል 4.6 ተራራ

ዝቅተኛ ቦታ፡ ዝቅተኛ ቦታ ማለት ትንሽ ከፍታ ባለው መሬት አካባቢ የሚገኝ ዝቀተኛ ቦታ ማለት ነው።



ሥዕል 4.7

ዝቅተኛ ቦታ

ሸለቆ፡ ከባህር ጠለል በታች በጣም ዝቅ ብሎ የሚገኝ የመሬት አቀማመጥ ነው።

ሸለቆ በሁለት ይከፈላል። እነርሱም፡-

- የወንዝ ሸለቆዎችና
- ትልቁ ስምጥ ሸለቆ ናቸው።



ሥዕል 4.8 የወንዝ ሸለቆዎች

## መልመጃ 4.4

ሀ. የሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ትክክል የሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ።

1. በመሬት አቀማመጥ አይነቶች መካከል የመሬት ከፍታ ልዩነት አለ።
2. ፕላቶ በከፍተኛ የመሬት አቀማመጥ አይነት ውስጥ ይገኛል።
3. ከፍተኛ ቦታ ኮረብታ ብቻ ያለው ነው።

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጥ/ጪ።

1. ከሚከተሉት የመሬት አቀማመጥ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ያለው የቱ ነው?

   ሀ. ሸለቆ ለ. ኮረብታ ሐ. ዝቅተኛ ቦታ

2. አነስተኛ ከፍታ ያለው የመሬት አቀማመጥ የቱ ነው?

   ሀ. ኮረብታ ለ. ፕላቶ ሐ. ዝቅተኛ ቦታ

3. አናቱ ሜዳማ/ዝርግ/ የሆነው የመሬት አቀማመጥ የቱ ነው?

   ሀ. ፕላቶ ለ. ኮረብታ ሐ. ተራራ

ሐ. ባዶ ቦታ ሙላ/ዪ።

1. ከአንድ አካባቢ ከፍ ብሎ የሚታይ የመሬት አቀማመጥ ይባላል።
2. በአንድ አካባቢ የመሬት አቀማመጥ ውስጥ በጣም ዝቅ ብሎ የሚገኝ መሬት ይባላል።

## የመሬት አቀማመጥ በአካባቢ ህብረተሰብ ላይ የሚፈጥረው ተጽዕኖ

የውይይት ጥያቄ

በአካባቢያችሁ የመሬት አቀማመጥ በህብረተሰቡ ኑሮና ሥራ ላይ ያለውን ተጽዕኖ የቀበሌያችሁን የግብርና ባለሙያ በመጠየቅ በክፍል ተወያዩበት።

ከፍታ በአካባቢ በህብረተሰብ ላይ ያለው ተጽዕኖ

ሠንጠረዥ 4.1 ከፍታ ያለው ተጽዕኖ

ሠንጠረዥ **4.1** ከፍታ ያላቸው መሬቶች ጥቅምና ጉዳት

| ከፍታ ያለው የመሬት ጥቅም | ከፍታ ያለው መሬት ጉዳት |
|---|---|
| • በቂ ዝናብና ሙቀት ስላለው ለእርሻ አመቺ ነው | • ከፍታ ያላቸው ብዙ ኮረብቶች አሏቸው. |
| • የወንዞች ተፈሰስ/ምንጭ ናቸው | • ለእርሻ የሚሆን መሬት የላቸውም |
| • እጽዋት ስላላቸው ለቱሪዝም መስህብ ውበት አላቸው | • ከፍታ ያለው ደጋማ መሬት በረዶና ቅዝቃዜ አላቸው |
| • ለእርሻ የሚሆን ለም አፈር አላቸው | • ከፍታ ያለው መሬት ለአፈር መሸርሸር /መጠረግ የተጋለጠ ነው |
| • በክልሎች ወይም በአገራት መካከል እንደ ድንበር መገልግል የመሳሰሉ | • ውጣ ውረድ ስለሚበዛበት ለመጓጓዣና ለግንኙነት አስቸጋር ነው |

በአጠቃላይ ከፍታ ያላቸው መሬቶች በዝናብና ሙቀት ሁኔታ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አላቸው። የአካባቢ አየር ንብረቱ ደግሞ

- በሚመመረት የእህል ዓይነት
- በልብስ ዓይነትና
- በህብረተሰቡ የመኖሪያ ቤት ዓይነት ላይ ተፅዕኖ አለው።

## ዝቅተኛ /ረባዳ/ መሬት በህብረተሰቡ ላይ ያለው ተፅዕኖ

## ሠንጠረዥ **4.2** የዝቅተኛ መሬት ጥቅምና ጉዳት

FF

| የዝቀተኛ መሬት ጥቅም | የዝቅተኛ መሬት ጉዳት |
|---|---|
| ለቤት እንስሳት እርባታ አመቺ ነው። ለእርሻም አመቺ ነው። | አነስተኛ ዝናብና ከፍተኛ ሙቀት አለው። ስለዚህ እርሻን በስፋት ለማከናወን አመቺ አይደለም። |
| ለመስኖ እርሻ አመቺ ነው።<br>ለሠፈራ አመቺ ነው። | ለዝናብ ውሃ ጎርፍ የተጋለጠ ነው። |
| ለመኪና መንገድ መሥሪያ።<br>ለመሳሰሉት አመቺ ነው። | እንስሳንና ሰውን የሚይዙ በሽታዎችና የመሳሰሉት መኖራቸው። |

## መልመጃ **4.5**

**ሀ.** ከዚህ በታች ያሉት ዐረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆኑ ደግሞ ሀሰት በማለት መልስ/ሺ።

1. ኮረብታ መሬት ረባዳ መሬት የለውም።

2. የመሬት አቀማመጥ ሁኔታ በኀብረተሰብ ኑሮ ላይ ተፅዕኖ የለውም።

3. የመሬት አቀማመጥ በዝናብና በሙቀት ሁኔታ ላይ ተፅዕኖ አለው።

**ለ.** ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጥ/ጪ።

1. የከፍተኛ መሬት ተፅዕኖዎችን ሁለቱን ጥቀስ/ሺ።

2. ከዝቀተኛ መሬት ተፅዕኖዎች ውስጥ ሁለቱን ጥቀስ/ሺ።

# 4.3 በወረዳችን /በከተማችን/ ውስጥ የሚገኙ ተቋማት

ፕሮጀክት **4.2**

| |
|---|
| 1. በወረዳችሁ ውስጥ የሚገኙ ለአካባቢ ኀብረተሰብ የተለያዩ ጥቅሞችን የሚሠጡ ተቋማትን የሚያውቁ ሰዎችን በመጠየቅ የተቋማቱን ስሞች ዘርዝሩ። |
| 2. በእነኚህ ተቋማት ላይ ተወያዩ። |
| 3. ከላይ የዘረዘራችሁትን ተቋማት የመንግሥትና የግል በማለት ከለያችሁ በኋላ ተወያዩባቸው። |

ለኀብረተሰባችን የተለያዩ አገልግሎቶች የሚሠጡ ተቋማት በሦስት

ይከፈላሉ።

እነርሱም፣

- የመንግሥት ተቋማት
- መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትና
- የግል ተቋማት ናቸው።

## የወረዳችን /የከተማችን/ የመንግሥት ተቋማት

## የወረዳችን /የከተማችን/ አስተዳደር

በወረዳ /በከተማ/ መስተዳድር የሚከናወኑ ሥራዎች የሚከተሉት ናቸው። እነርሱም፡-

- ጽ/ቤቶችንና የተለያዩ ለኀብረተሰቡ የሚያገለግሉ ሌሎች ተቋማትን መምራት
- ኀብረተሰቡ እንደ ትምህርት፣ ጤና፣ መጓጓዣ፣ ፋይናንስ የመሳሰሉ ማህበራዊ አገልግሎቶችን ማግኘቱን መከታተል

- ኅብረተሰቡን በማደራጀት የልማት ሥራዎች በትጋት እንዲከናወኑ አስፈላጊውን እገዛ መስጠት
- የኅብረተሰቡን ደህንነት መጠበቅና የመሳሰሉት ናቸው።

## የወረዳ /የከተማ/ ፍርድ ቤት



ሥዕል **4.9** ዳኞች ለኅብረተሰቡ የፍትህ ውሳኔ ሲሰጡ

የወረዳ /የከተማ/ መስተዳድር ፍርድ ቤት አንድ ወንጀል የሠራ ወይም ሕግ የተላለፈ ሰው /ተቋም/ ተከሶ ጉዳዩን መርምሮ ብይን የሚሠጥ አካል ነው።

## የወረዳ /የከተማ/ መስተዳድር የፖሊስ ጽ/ቤት

ከወረዳ /ከተማ/ መስተዳድር ፖሊስ የሥራ ድርሻዎች ውስጥ ጥቂቶቹ እንደሚከተሉት ይሆናል። እነርሱም፣

- ወንጀልን መከላከልና ሕግን ማስከበር
- ወንጀል ሠርቶ የተጠረጠረ /የተከሰሰውን/ ሰው መርምሮ ለችሎት ማቅረብ
- የኅብረተሰቡን ሰላምና መረጋጋት መጠበቅ
- ኅብረተሰቡን የትራፊክ ሕግ ማስተማርና ሕጉን እንዲያከብሩ ማድረግ የመሳሰሉት ናቸው።

## የወረዳ /የከተማ/ መስተዳድር ትምህርት ቤቶች ጽ/ቤት

የወረዳ ወይም የከተማ መስተዳድር ትምህርት ቤቶች ጽ/ቤት የሚከተሉት ተግባራትን ያከናውናሉ። እነርሱም፣

- የትምህርት ቤቶችን ግንባታና የትምህርት ሥርጭትን መከታተልና ማስፈጸም
- የመምህራን ምደባና ዝውውር ማከናወን
- ለትምህርት ቤቶች መጽሐፍት ማሠራጨት
- የመማር ማስተማር ሂደቱን መከታተልና መቆጣጠር የመሳሰሉት ናቸው።

በወረዳ /በከተማ/ ማስተዳድር ውስጥ በሚገኙ ሌሎች መንግሥታዊ ተቋማትም ይኖራሉ። እነርሱም

- የጤና ጥበቃ ጽ/ቤት
- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት
- የሲቭል ሰርቪስና መልካም አስተዳደር ጽ/ቤት
- የወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ጽ/ቤት
- የሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ
- የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ጽ/ቤት

## በወረዳችን /በከተማችን/ መስተዳድር ውስጥ የሚገኙ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት

*መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በትምህርት፣ በጤና፣ በንፁህ የመጠጥ ውሃ፣ በስነ ፆታና በሌሎችም ተግባራት ላይ በመሠማራት ኅብረተሰቡን ለመርዳት የሚንቀሳቀሱ ናቸው።*

*መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃን እንደምሳሌ መውሰድ እንችላለን።*



ሥዕል

*4.1* ፀ የቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ ማህበር ለኅብረተሰቡ እርዳታ ሲያደርጉ

## የግል ተቋማት

የግል ተቋማት በግለሰቦች በጐ ፍላጐትና ወጪ ተቋቁመው በማምረት ተግባር ወይም ለኅብረተሰቡ የተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ተግባራት ላይ የተሠማሩ ናቸው። ለምሳሌ:

- የግል ትምህርት ቤቶች
- የግል ሆቴሎች
- የግል የመጓጓዣና የትራንስፖርት ማህበራት
- የግል የተለያዩ የእቃ መሸጫ ሱቆች
- የግል የቡና፣ የአትክልትና የፍራፍሬ እርሻዎች
- የግል የሕንፃ ግንባታና የመንገድ ሥራ ተቋራጮች
- የግል ክሊኒኮችና ፋርማሲዎች
- የተለያዩ የግል የማምረቻ ፋብሪካዎችና የመሳሰሉት ናቸው።

*መልመጃ* **4.6**

**ሀ.** ከዚህ በታች ያሉት ዐረፍ ተነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ።

1. ሁሉም ተቋማት ኀብረተሰቡን ያገለግላሉ።
2. ፍርድ ቤትና የፖሊስ ጽ/ቤት የሥራ ግንኙነት አሏቸው።

**ለ.** ከዚህ በታች ላሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጥ/ጪ።

1. ከሚከተሉት ውስጥ መንግሥታዊ ያልሆነ ተቋም የቱ ነው?

   ሀ. የወረዳ ትምህርት ቤቶች ጽ/ቤት

   ለ. የቀይ መስቀል ማህበር

   ሐ. የፖሊስ ጽ/ቤት

2. በወንጀል የተጠረጠረውን ሰው ለሕግ የሚያቀርበው አካል የቱ ነው?

   ሀ. ፍርድ ቤት ለ. ከሳሽ ሐ. የፖሊስ ጽ/ቤት

**ሐ.** ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጥ/ጪ።

1. ከግል ተቋማት ውስጥ ሦስቱን ጥቀስ/ሺ።

2. ከመንግሥታዊ ተቋማት ውስጥ አራቱን ጥቀስ/ሺ።

3. መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ውስጥ ሁለቱን ጥቀስ/ሺ።

## 4.4 የወረዳችን /የከተማችን/ መስተዳድር የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች

የሰው ልጅ ለመኖር የሚያስፈልጉትን እንደ ልብስ፣ ምግብ፣ መጠለያና የመሳሰሉትን ለማግኘት የሚደረጉ ተግባራት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ይባላሉ።

### ተግባር 4.2

በወረዳ /በከተማችሁ/ መስተዳድር ውስጥ የሚከናወኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አይነቶችን በመዘርዘር ተወያዩበት።

ግብርና

ግብርና ምንድነው?




ሥዕል 4.11


ለእህል ምርትና ለከብት እርባታ የሚደረጉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ግብርና ይባላል።

ግብርና በሁለት መንገድ ይከናወናል። እነርሱም ባህላዊና ዘመናዊ የግብርና ዘዴዎች ናቸው።

ሥዕል 4.12 ባህላዊ የእርሻ ዘዴ









የእርሻ መኪናዎች /ትራክተሮች/ እህልን የሚያጭድ ማሽን /ኮምባይነር/

ሥዕል 4.13 ዘመናዊ የግብርና ዘዴዎች

## የግብርና ጥቅሞች

- ግብርና የምግብ ምንጭ ነው።
- ግብርና የኢንዱስትሪ ጥሬ እቃዎች ምንጭ ነው። ለምሳሌ ሸንኮራ አገዳ ጥጥና የሻይ ቅጠል የፋብሪካ ጥሬ እቃዎች ናቸው።
- ግብርና የውጭ ምንዛሪ ገቢ ምንጭ ነው። ለምሳሌ የኢትዮጵያ የገቢ ምንጭ ከቡና፣ ከቆዳና ከመሳሰሉት ይገኛል።

- ግብርና የአገራችን ሕዝቦች በብዛት የሚሳተፉበት ተግባር ነው።

## ንግድ

ንግድ ምንድ ነው? ንግድ የእቃዎች ግብይት የሚከናወንበት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ነው፣




ሥዕል 4.14 የእቃዎች ግዥና ሽያጭ ሂደት /ገበያ/

## የንግድ ጥቅሞች

አንድ ኅብረተሰብ ሁሉን ነገር እራሱ አምርቶ ፍላጐቱን ማሟላት አይችልም። ስለዚህ ንግድ፣

- በአንድ አካባቢ የማይመረቱ/የማይገኙ/ ነገሮችን ከሌሎች አካባቢ በግዥና በሽያጭ ያስገኛል።
- አካባቢን ከአካባቢ ለማገናኘት እድል ይፈጥራል።
- ለሃሳብና ባህል ልውውጥ እድል ይፈጥራል።
- ለኅበረተሰቡ አባላት የሥራ እድል ይፈጥራል።
- ለከተማ እድገት አስተዋፅኦ ማበርከትና ለመሳሰሉት ይጠቅማል።

## መጓጓዣ

መጓጓዣ ምንደነው?
የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ከቦታ ቦታ ሰዎችንና እቃዎችን ማንቀሳቀስ መጓጓዣ ይባላል።

መጓጓዣ በሁለት ይከፈላል። እነርሱም፡-

1. ባህላዊ መጓጓዣና
2. ዘመናዊ መጓጓዣ ናቸው።

## 1. ባህላዊ መጓጓዣዎች

ባህላዊ መጓጓዣዎች የቤት እንስሳት እንደ አህያ፣ ፈረስ፣ በቅሎና ግመል በመሳሰሉት እቃና ሰዎችን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለማንቀሳቀስ ይረዳሉ።





ሥዕል 4.15 ባህላዊ የመጓጓዣ ዘዴ

## 2. ዘመናዊ መጓጓዣዎች:

ዘመናዊ መጓጓዣዎች እንደ መኪና፣ ባቡር፣ መርከብና አውሮፕላን ሲሆኑ እቃዎችንና ሰዎችን ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ ይረዳሉ።



Xiyyaaraa



Baaburaa



Konkolaataa



Doonii

ሥዕል 4.16 ዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች

### የመጓጓዣ ጥቅሞች

- እቃዎችን ከቦታ ቦታ ለማጓጓዝ ይጠቅማል።
- የተለያዩ አካባቢ ኅብረተሰብን ለማገናኘት ይጠቅማል።
- ለኅብረተሰብ አባላት የሥራ እድል ለመፍጠር ይጠቅማል።

### ኢንዱስትሪ

ኢንዱስትሪ ምንድነው?



ሥዕል 4.17

ጥሬ እቃዎችን ፋብሪካ ውስጥ በማስገባት ወደ አንድ ጠቃሚ ነገር የመቀየር ሂደት የኢንዱስትሪ ተግባር ነው። ለምሳሌ፣

- የሸንኮራ አገዳ → የስኳር ፋብሪካ → ስኳር
- ጥጥ → የልብስ ፋብሪካ → ልብስ

### የኢንዱስትሪ ጥቅሞች

- እቃዎችንና የተለያዩ መሣሪያዎችን ለኅብረተሰቡ ያመርታል።

ለምሳሌ፡ ሣሙና፣ ስኳር፣ ክብሪት፣ ካልሲ፣ ጫማ የመሳሰሉትን።

- በግብርና ውጤቶች በመጠቀም የግብርና ምርታማነትን ይጨምራል።
- የማምረቻ መሣሪያዎችን እንደ ማጭድ፣ ምስማር፣ ሲሚንቶና ለተለያዩ ጥቅም የሚውሉ ማሽኖችን ያመርታል።
- ለኅብረተሰብ አባላት የሥራ እድል መፍጠርና የመሳሰሉት ናቸው

## የእደ ጥበብና የጎጆ ኢንዱስትሪ

በአካባቢያችሁ የሚሠሩ የእደ ጥብብ ውጤቶች ምን ምን ናቸው?

በባህላዊ መንገድ እቃዎችን ሙያ ባላቸው ሰዎች ማምረት እደጥበብ ይባላል።







*ሥዕል 4.18 የእደ ጥበብ ሥራዎች*

ሠንጠረዥ **4.3** የእደጥበብ ሥራዎችና ምርቶቻቸው

| **የእደ ጥበብ ሥራ አይነቶች** | **ለምርት የሚውሉ ጥሬ እቃዎች** | **የሚመረቱ እቃዎች** |
|---|---|---|
| **የሸክላ ሥራ** | የሸክላ አፈር | እንስራ፣ ሲኒ፣ ድስት፣ ጀበና ምጣድ ወዘተ |
| **የቆዳ ሥራ** | የእንስሳት ቆዳ | ቁርበት ጠፍር፣ ቀበቶ፣ ስልቻ፣ ኮርቻ፣ የጠፍር አልጋ ወዘተ |
| **የሽመና ሥራ** | ጥጥ | የተለያዩ ልብሶች |
| **ስፌት** | ስንደዶ /ሰበዝ/ | መደብ፣ እርቦ፣ ሠፌድ፣ ቁና፣ ወንፊት ወዘተ |
| **የእንጨት ሥራ** | እንጨት | አልጋ፣ በትር፣ በር፣ ቤት፣ መቀመጫ፣ ጠረጴዛ ወዘተ |
| **የብረታ ብረት ሥራ** | ብረት | ቢላ፣ መጥረቢያ፣ ማረሻ፣ ወገል ወዘተ |

- እቃዎችን በአነስተኛ ዋጋ ማቅረብ
- በአካባቢ በሚገኙ ጥሬ እቃዎች በመጠቀም ምርት መስጠት
- ለዘመናዊ ኢንዱስትሪ መስፋፋት መሠረት መሆንና የመሳሰሉት ናቸው።

## መልመጃ **4.7**

ሀ**.** የሚከተሉት ዐርፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልስ/ሺ።

1. ማንኛውም ኅብረተሰብ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ አለው።
2. ግብርናና ኢንዱስትሪ ግንኙነት የላቸውም።
3. አህያና በቅሎ ለመጓጓዣ አገለግሎት ይጠቅማሉ።
4. አብዛኛው የገጠር ነዋሪ ሕዝብ አርሶ አደር ነው።

ለ. ከሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጥ/ጪ።

1. ግብርና ከሚከተሉት ውስጥ ለየትኛው ጥቅም ይውላል?

ሀ. ለምግብ ምንጭነት ሐ. ሁሉም መልስ ናቸው

ለ. ለገቢ ምንጭ

2. እቃዎች የሚገዙበትና የሚሸጡበት ቦታ ምን ይባላል?

ሀ. መሥሪያ ቤት ለ. ገበያ ሐ. ጤና ጣቢያ

3. ጥሬ እቃ የሆነው የቱ ነው;

ሀ. ጥጥ ለ. ስኳር ሐ. ክብሪት

4. የመጓጓዣ ጥቅም የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ኅብረተሰብን ከኅብረተሰብ ማገናኘት

ለ. እቃዎችን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ማጓጓዝ

ሐ. ሁሉም መልስ ናቸው።

5. ልብስን የሚያመርት የኢኮኖሚያዊ እንቅስቅሴ አይነት የቱ ነው?

ሀ. ኢንዱስትሪ ለ. ግብርና ሐ. ንግድ

ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መለስ ስጥ/ጪ።

1. ከንግድ ጥቅሞች ውስጥ ሦስቱን ጥቀስ/ሺ።
2. ከእደጥበብ ጥቅሞች ውስጥ ሦስቱን ጥቀስ/ሺ።
3. የቤተሰቦችህ ሥራ በየትኛው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ እንደሚመደብ ገለጽ/ጪ።

## የቴክኖሎጂ ውጤት መሣሪያዎችና ጥቅማቸው

በአካባቢያችሁ የሚገኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመዘርዘር በቡድን በመወያየት እንደየ ጥቅማቸው መድቧቸው።

### ሬድዮ

ሬድዮ የአገር ውስጥና የውጭ መረጃዎችን በማሠራጨት ለኅብረተሰቡ አገለግሎት ይሠጣል።




ሥዕል 4.19 ሬድዮ

### ቴሌቪዥን

በቴሌቪዥንና በሬድዮ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው;

ቴሌቪዥን በድምፅና በምስል መረጃዎችን በማሠራጨት ለኅብረተሰቡ አገለግሎት ይሠጣል።




ሥዕል 4.20 ቴሌቪዥን

## የኤሌክትሪክ ምድጃ /ምጣድ/

የኤለክትሪክ ምድጃ/ምጣድ/ ምግብ ለማብሰል የሚያገለግል መሣሪያ ነው፡፡





የኤሌክትሪክ ምጣድ የኤሌክትሪክ ምድጃ /እስቶቭ/

ሥዕል 4.21 የኤሌክትሪክ ምጣድና ምድጃ

## ጀኔሬተር

ጀኔሬተር በነዳጅ ኃይል በመንቀሳቀስ ኤሌክትሪክ የሚያመነጭ መሣሪያ ነው፡፡




ሥዕል 4 .22 ጀኔሬቴር

## ፍሪጅ /ማቀዝቀዣ/

### ፍሪጅ ምንድነው?


ፍሪጅ የማቀዝቀዣ ማሽን ነው። በፍሪጅ ውስጥ እንደ ሥጋ፣ ወተት፣ አትክልት፣ ፍራፍሬና የመሳሰሉት ምግቦች ሳይበላሹ /መጥፎ ሽታ ሳያመጡ ለረጅም ጊዜ ይቆያሉ።





ሥዕል **4.23** ፍሪጅ /ማቀዝቀዣ/

## የኤሌክትሪክ ካውያ

የኤሌክትሪክ ካውያ ታጥቦ የደረቀ ልብስን ለመተኮስ







*ሥዕል 4.24 የታጠበ ልብስን መተኮስ።*

ስልክ

ስልክ ምን ዓይነት መሣሪያ ነው? ስልክ የመገናኛ መሣሪያ ነው።

ሁለት የስልክ ዓይነቶች አሉ። እነርሱም

- ቋሚ የቤት /የመሥሪያ ቤት/ ስልክና
- ተንቀሳቃሽ ስለክ ናቸው።.





*ሥዕል 4..25 ቋሚ የቤት/የቢሮ ስልክ* *ሥዕል 4..25 ተንቀሳቃሽ ስልክ*

የውይይት ጥያቄ

ተንቀሳቃሽ ስልክ /ሞባይል/ ምን ጥቅም እንዳለው ተወያዩበት

*መልመጃ* **4.8**

ሀ**.** ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን *መ*ልስ ምረጥ/ጪ።

1. ከሚከተሉት ውስጥ ልዩ የሆነው የቱ ነው?

    ሀ. የኤሌክትሪክ ምድጃ

    ለ. ሬድዮ ሐ. ቴሌቪዥን

2. ምግብ ሳይበላሽ እና መጥፎ ሽታ ሳያመጣ ለረዥም ጊዜ የሚያቆይ መሣሪያ ምንድነው?

    ሀ. ጀኔሬተር

    ለ. ፍሪጅ /ማቀዘቀዣ/ ሐ. የኤሌክትሪክ ካውያ

3. የኤሌክትሪክ ጉልበት ለማመንጨት የሚያገለግለው መሣሪያ የቱ ነው?

    ሀ. ተንቀሳቃሽ ስልክ /ሞባይል/

    ለ. ሬድዮ ሐ. ጀኔሬተር

## ለወረዳችን /ለከተማችን/ ልማት የሥራ አስፈላጊነት

የውይይት ጥያቄ

- *ሥራ ለምን ያስፈልጋል?*

ሰዎች በተለያዩ *ሥራ* ላይ *መሠማራታቸው* ምን ጥቅም አለው? ለምሳሌ፡ የፖሊስ፣ የጤና የማስተማርና የመሳሰሉት

እያንዳንዳችሁ በምን *ሥራ* ላይ *መሠማራት* እንደምትፈልጉ በመፃፍ *ሥራው* ለቤተሠብ እና ለአካባቢያችሁ ማኅበረሰብ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ተወያዩበት። *ሥራ* የኑሮ *መሠረት* ነው። በተለያዩ *ሥራ* ላይ የተሠማሩ ሰዎች ለመኖር *መሠረታዊ* የሆኑ ነገሮች እንደ ምግብ፣ ልብስ እና *መ*ጠለያ *ያገኛሉ*።

የሰው ልጆችን ከሌሎች እንስሳት ልዩ ከሚያደረጉት ነገሮች ውስጥ አንዱ ሠርቶ በመኖሩ ነው።

*ሥዕል 4.26 በተለያዩ ሥራዎች ላይ መሣተፍ*

ማንኛውም ሰው ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ብቻውን በማምረት ማሟላት አይችልም። ስለሆነም የተለያዩ ስዎች በተለያዩ ሥራ ላይ በመሠማራት የድርሻቸውን መወጣት አለባቸው። ለወረዳችን /ለከተማችን/ ልማት ማንኛውም ሰው ባላው ሙያ እና ችሎታ ሥራ ላይ መሣተፍ በጣም አስፈላጊ ነው።

ለአካባቢያችን ሕብረተሠብ ማንኛውም አይነት ሥራ ጥቅም አለው። ለምሳሌ እርሶ አደር ካላረሰ የምግብ እህል አይገኝም፣ የጤና ባለሙያ የጤና አገልግሎትን ካልሠጠ የታመመ ሰው ሕክምና አያገኝም።
በተመሳሳይ መልኩ መምህሩ ካላስተማረ እውቀት አይገኝም፤ ፖሊስ በጥበቃ ሥራ ላይ ካልተሠማራ የአካባቢ ሰላም /ደህንነት/ አይጠበቅም። ስለዚህ ማንኛውም ሥራ ለሕብረተሰባችን አስፈላጊ ስለሆነ መከበር አለበት።

*መልመጃ* **4.9**

ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጥ/ጪ።

1. የአንድ ሕብረተሰብ ልማት የሚያድገው በምንድን ነው?

   ሀ. በስራ ለ. በውይይት ብቻ ሐ. ወጪን በመቀነስ

2. የሰው ልጅን ከሌሎች እንስሳት ልዩ የሚያደርገው ምንድነው?

ሀ. የሕዝብ ብዛት　　　　　　ሐ. አብሮ መኖሩ

ለ. በተለያየ ስራ ላይ መሠማራቱ

3. ለሕብረተሰባችን የሚያስፈልግ የልማት ሥራ የቱ ነው;

ሀ. ንግድ　　　ለ. ግብርና　　　　　ሐ. ሁሉም መልስ ነው።

የቃላት ትርጉም

መገኛ፡ አንድ በመሬት ላይ ያለ ወይም አንድ ነገር የሚገኝበት ቦታ

ኃይል: አንድን ነገር የመሥራት ችሎታ

ወረዳ፡ ብዙ ቀበሌዎች ያሉት የአንድ አገር ክፍል

ተፅዕኖ: በአንድ ነገር ላይ ጫና መፍጠር

ጐልማሳ: በአካል እና በአዕምሮ የጐለበተ ሰው

የእድሜ ክልል: በአንድ የእድሜ ወሰን ውስጥ የሚገኙ ወይም የሚቀራረቡ ሰዎች

እቅድ፡ አንድን ነገር በቅደም ተከተል ለማከናወን የሚጠቅም ዘዴ /አንድን ተግባር ከግብ ለማድረስ የሚያስችል ዘዴ/

ልማት፡ የእድገት ደረጃ መሻሻል

የመብት ጥሰት፡ በሰው አካልና አእምሮ ላይ ጉዳት ማድረስ

መረጃ /ፕሮፋይል/፡ አንድን ነገር ከትንሽ ወደ ትልቅ በአንድ ላይ በማካተት የሚያሳይ ምስል

ባሕላዊ ግብርና፡ በባሕላዊ መሣሪያና ዘዴ የሚከናወን ግብርና

ቁና: ባሕላዊ የመስፈሪያ እቃ.
ተፈጥሯዊ ክስተቶች: በተፈጥሮ በአካባቢያችን የሚከሰቱ ነገሮች
ቴክኖሎጂ፡ አንድን ነገር ለማከናውን የሚያግዝ እውቀት፣ ችሎታ፣ ልማድ፣ ሙያ አጣምሮ የያዘ ሣይንስ ነው።
የጐጆ ኢንዱስትሪ፡ የመኖሪያ አካባቢን ያማከለ በእጅ የሚሠራ የእደ ጥበብ ሥራ ነው።